ያዕቆብ 2፡14-26

«ወንድሞቼ ሆይ፥ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ፥ ከእናንተ አንዱም፦ - በደኅና ሂዱ፥ እሳት ሙቁ፥ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባተሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል? እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።

«ነገር ግን አንድ ሰው፦ - አንተ እምነት አለህ እኔም ሥራ አለኝ፤ እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ፥ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ ይላል። እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል። አንተ ከንቱ ሰው፥ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? አባታችን አብርሃም ልጁን ይሰሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራ ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበር፥ በሥራም እምነት እንደተፈጸመ ትመለከታለህን? መጽሐፍም፦ - አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ። ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ። እንደዚሁም ጋለሞታዪቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችም? ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁም ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።»

-6-

ሐሰተኛ እምነት

እምነት በክርስትና ሕይወት ውስጥ ቁልፍ የሆነ መሠረታዊ ትምህርት ነው። ኃጢአተኛ የሚድነው በእምነት ነው (ኤፌ. 2፡8-9)። አማኝ መኖር ያለበትም በእምነት ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡7)። ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም (ዕብ. 11፡6)። ያለ እምነት የምናደርገው ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው (ሮሜ 14፡23)።

አንድ ሰው እንዲህ አለ፡- እምነት «ያለምንም ማረጋገጫ አንድን ነገር ማመን ማለት አይደለም፤ ነገር ግን የሚያስከትለው ነገር ምንም ይሁን መታዘዝ ማለት ነው»። ዕብ. 11 በምታነብበት ጊዜ የሚከፍሉት ዋጋ ምንም ይሁን በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚራመዱ ወንዶችና ሴቶች የእግዚአብሔር ሰዎችን ትመለከታለህ። እምነት በግልጽ የማይታወቅ እንደ ደመና የተሸፈነ ዓይነት ስሜትና ከእኛ የመነጨ ወይም ልንሠራው የሚገባ ነገር አይደለም። እምነት የእግዚአብሔር ቃል እውነት የመሆኑ የዋስትና ስሜትና በዚያ ቃል መኖር በረከትን እንደሚያስገኝ እርግጠኛ መሆን ነው።

በዚህ አንቀጽ ያዕቆብ በእምነትና በመልካም ሥራዎች መካከል ስላለው ግንኙነት ይናገራል። ይህ ርእስ እጅግ ጠቃሚ ርእስ ነው። ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ ከተሳሳትን ዘላለማዊ ደኅንነታችንን አደጋ ላይ እንጥለዋለን። ሰውን በእርግጥ የሚያድነው ምን ዓይነት እምነት ነው? መልካም ሥራዎችን መፈጸም ለደኅንነት አስፈላጊ ነውን? አንድ ሰው እውነተኛውን የሚያድን እምነት እየተለማመደ እንደሆነ ለማወቅ የምንችለው እንዴት ነው? ያዕቆብ ለእነዚህ ጥያቄዎች የሰጠው መልስ ሦስት ዓይነት እምነቶች እንዳሉና ከእነዚህ መካከል አንዱ ብቻ እውነተኛ እምነት እንደሆነ ነው።

የሞተ እምነት (2፡14-17)

በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን እንኳ የሚያድን እምነት እንዳላቸው የሚናገሩ ደኅንነትን ግን ያላገኙ ሰዎች ነበሩ። አንድ እውነት ባለበት ሥፍራ ሁሉ ያንን እውነት የሚመስሉ ነገር ግን ያልሆኑ ነገሮች ይገኛሉ። ጌታ ኢየሱስ እንዲህ የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፡- «በሰማያት

ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» (ማቴ. 7፡21)።

የሞተ እምነት ያላቸው ሰዎች ተግባርን በንግግር ይተኩታል። በጸሎትም ሆነ በምስክርነት ጊዜ ትክክለኛ ቋንቋና ዐረፍተ ነገር ይናገራሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስም ትክክለኛ ጥቅሶችንም ሊጠቅሱ ይችላሉ። ነገር ግን ኑሮአቸው ከንግግራቸው ጋር የሚጣጣም አይደለም። ንግግራቸው የመልካም ሥራዎችን ያህል ጥሩ እንደሆነ ያስባሉ፥ ግን ትክክል አይደለም።

ያዕቆብ ስለዚህ ጉዳይ ቀላል መግለጫን ይሰጣል። አንድ ደሀ አማኝ ጥሩ ልብስ ሳይለብስና ተርቦ ወደ ጉባኤ ይመጣል። የሞተ እምነት ያለው ሰው ይህንን እንግዳ ቢያየውም ምንም አያደርግለትም። ጥቂት የማስመሰል ቃላት ብቻ ይናገራል፥ «ሂድ፥ እሳት ሙቅ፥ ጥገብም» (2፡16)። ይህ እንግዳ ሰው ግን እንደተራበና እንደተራቆተ በመጣበት ይመለሳል።

ለሚያምን ሆነ ለማያምን ምግብና ልብስ መሠረታዊ ፍላጎት ነው። «ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፥ እርሱ ይበቃናል» (1ኛ ጢሞ. 6፡8)። «እንግዲህ፥ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፥ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና» (ማቴ. 6፡31-32)። ያዕቆብ እነዚህን መሠረታዊ ፍላጎቶች ወደ እግዚአብሔር ባቀረበው ጸሎት አካትቶአቸው ነበር። «እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን ... የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ ...» (ዘፍ. 28፡20)።

ማንም ይሁን ማን እውነተኛ አማኞች እንደመሆናችን መጠን በሚያስፈልጓቸው ነገሮች ሁሉ መርዳት አለብን። «እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ» (ገላ. 6፡10)። «እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንድ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል» (ማቴ. 25፡40)።

አንድን ችግረኛ መርዳት የፍቅር መግለጫ ነው፤ እምነት የሚሠራው ደግሞ በፍቅር ነው (ገላ. 5፡6)። ሐዋርያው ዮሐንስ ለእንደዚህ ዓይነቱ የመልካም ሥራዎች ገጽታ ትኩረት በመስጠት ተናግሯል። «ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፥ ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን

የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ልጆቼ ሆይ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ» (1ኛ ዮሐ. 3፡17-18)። በመልካሙ ሳምራዊ ታሪክ ውስጥ ካህኑና ሌዋዊው ሁለቱም ሃይማኖታዊ ትምህርት ነበራቸው፤ በመንገድ ዳር ወድቆ በሞትና በሕይወት መካከል የነበረውን ሰው ለመርዳት ግን አልተነሣሡም (ሉቃ. 10፡25-37)። እነዚህ ሰዎች እምነት አለን በማለት ለእምነታቸው እውነተኛነት ሊከራከሩ ይችላሉ፤ እምነታቸው ግን በፍቅር የተገለጠ አልነበረም።

በቁጥር 14 ላይ ያለው ጥያቄ «እንዲህ ዓይነቱ እምነት ሊያድን ይችላል?» ተብሎ ሊነበብ ይገባዋል። ይህ ምን ዓይነት እምነት ነው? በተግባራዊ ሥራዎች የማይገለጥ እምነት ነው። መልሱ ሊያድን አይችልም መሆን አለበት። በተለወጠ ሕይወትና በመልካም ተግባራት የማይገለጥ እምነት ሐሰተኛ እምነት ነው። እንዲህ ዓይነት እምነት የሞተ ነው። «እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው» (ያዕ. 2፡17)። ታላቁ የሥነ መለኮት ትምህርት ሊቅ የነበረው ጆን ካልቪን እንዲህ በማለት ጽፏል፡- «የሚያጸድቅ እምነት ብቻ ነው፤ ነገር ግን የሚያጸድቅ እምነት ብቻውን ሊሆን አይችልም» በቁጥር 17 ላይ «ብቻ» የሚለው ቃል ትርጉም «በራሱ» ማለት ነው። እውነተኛ የሚያድን እምነት በራሱ ብቻውን ሊሆን አይችልም። ሁልጊዜ ሕይወትን ያመጣል፤ ይህም ሕይወት መልካም ተግባርን ያፈራል።

የሞተ እምነት ያለው ሰው እውቀት ብቻ ነው ያለው። በአእምሮው የደኅንነትን መሠረታዊ ትምህርት ያውቃል፤ ነገር ግን እራሱን ለእግዚአብሔር ሰጥቶ አያውቅም፤ ለደኅንነቱም በክርስቶስ አልታመነም። ትክክለኛ ቃሎችን ያውቃል፤ ቃሎቹና ተግባሩ ግን ጨርሶ አልተስማሙም። በክርስቶስ ማመን ሕይወትን ይሰጣል (ዮሐ. 3፡16)፤ ሕይወት ባለበት ደግሞ ዕድገትና ፍሬ ማፍራት አለ። በዚህ አንቀጽ ውስጥ ሦስት ጊዜ ያዕቆብ «ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ» እንደሆነ በመናገር ያስጠነቅቃል (2፡17፣ 20፣ 26)።

በእውቀት ላይ ብቻ ከተመሠረተ እምነት ልንጠነቀቅ ይገባል። አንድ ሰው 220 ቮልት ጉልበት ካለው የኤሌትሪክ ገመድ ጋር ተገናኝቶ ምንም ሳይሆን ሊቀር እንደማይችል ሁሉ ማንም ሰው ወደ ክርስቶስ በእምነት መጥቶ እንደ ቀድሞው ምንም ሳይለወጥ ሊቀር አይችልም። «ልጁ ያለው ሕይወት አለው፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም» (1ኛ ዮሐ. 5፡12)። የሞተ እምነት የሚያድን እምነት

አይደለም። የሞተ እምነት አንድ ሰው ስለ ዘላለም ሕይወት የተሳሳተ ዋስትና እንዲሰማው የሚያደርግ አሳሳች እምነት መሳይ ነገር ነው።

የአጋንንት እምነት፥ (2፡18-19)

ያዕቆብ እነዚህ በራሳቸው የረኩ አንባቢዎችን ለማስደንገጥ አጋንንቶችን እንደ ምሳሌ ይጠቀማል። በቅርቡ ቤተ ክርስቲያን የአጋንንቶችን ሕልውና እውነትነትና ተግባራቸውን እንደገና ልትገነዘብ ችላለች። ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ባገለገለበት በአብዛኛው ጊዜ ከሰዎች አጋንንቶችን ያወጣ ነበር። ይህንንም ኃይል ለደቀ መዛሙርቱ ሰጥቶ ነበር። ጳውሎስ በአገልግሎቱ ብዙ ጊዜ ከአጋንንት ኃይል ጋር ታግሎአል። በኤፌ6፡10-20 ደግሞ የቀድሞ ክርስቲያኖች ከዚህ ዓለም የከፉት መንፈሳዊያን ኃይላት እንዲጠበቁ የእግዚአብሔርን ጥበቃ መጠየቅ እንዳለባቸው ያሳስባቸዋል።

አጋንንት እንኳ እምነት እንዳላቸው መስማት ሰዎችን ያስደነግጣቸዋል! አጋንንት የሚያምኑት ምንድን ነው? በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ሕልውና ያምናሉ። አጋንንት እግዚአብሔር የለሾች (ኤቲስት) ወይም ስለ እግዚአብሔር ምንም ነገር ሊታወቅ አይችልም የሚሉ (አግኖስቲኮች) አይደሉም። በክርስቶስ መለኮትነት ያምናሉ። ክርስቶስ በምድር በነበረበት ጊዜ ከእርሱ ጋር ሲገናኙ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ይመሰክሩ ነበር (ማር. 3፡11-12)። የቅጣት ስፍራ ስለ መኖሩም ያምኑ ነበር (ሉቃስ 8፡31)። ኢየሱስ ክርስቶስም ፈራጅ መሆኑን ያውቁ ነበር (ማር. 5፡1-13)። ለቃሉ ኃይልም ይገዛሉ።

«እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው» (ዘዳግ. 6፡4)። ይህ እግዚአብሔርን የሚፈራ የማንኛውም አይሁዳዊ የየቀን የእምነት መግለጫ ነው። «እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል» (ያዕ. 2፡19)። የሞተ እምነት ያለው ሰው የሚነካው በአእምሮው ብቻ ነው፤ አጋንንት ግን በስሜታቸው ጭምር ይነካሉ፤ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል። ማመንና መንቀጥቀጥ ግን ለደኅንነት የሚያበቁ አይደሉም። አንድ ሰው በአእምሮው እውቀት ሊበራለት፥ በልቡም የትነቃቃ ሆኖ እንኳ ለዘለዓለም ሊጠፋ ይችላል። እውነተኛ የሚያድን እምነት ከዚህ የላቀ ነገር የሚከናወንበት ሊታይና ሊታወቅ የሚችል ነገር የያዘ ነው፤ ይህም የተለወጠ ሕይወት ነው።

«እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ» ያዕቆብ ያቀረበው አማራጭ ነበር። «እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ» (ያዕ. 2፡18)።

አንድ ሰው ያለ መልካም ተግባር እምነቱን እንዴት ሊያሳይ ይችላል? የሞተ ኃጢአተኛ መልካም ነገር ሊያደርግ ይችላል? አይችልም! በክርስቶስ በምንታመንበት ጊዜ «እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀደሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» (ኤፌ. 2፡10)። ክርስቲያን መሆን በክርስቶስ መታመንና ለክርስቶስ መኖርን የሚያካትት ነገር ነው፤ ሕይወትን ትቀበላለህ፤ ከዚያም ሕይወትን ትገልጣለህ። ፍሬ የማያፈራ መካን እምነት የማያድን እምነት ነው። በቁጥር 20 ላይ «የሞተ» ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል ምንም ወለድ እንደማያስገኝ የተቀመጠ ገንዘብ፥ መካን፥ ፍሬ የማያፈራ ወይም ሥራፈት የሚል ትርጉም አለው።

ያዕቆብ ኃጢአተኛን ሊያድኑ ጨርሶ ስለማይችሉት ሁለት ዓይነት እምነቶች ይገልጻል። እነርሱም የሞተ እምነት (የአእምሮ ብቻ) እና አጋንንታዊ እምነት (አእምሮአዊና ስሜታዊ) ናቸው። ያዕቆብ በዚህ ክፍል የሚያቀርበውን ትንተና የሚያጠቃልለው ኃጢአተኛን ሊያድን ስለሚችለው እምነት ማለትም ኃይል ስላለው እምነት በመናገር ነው።

ኃይል ያለው እምነት፥ (2፡20-26)

ኃይል ያለው እምነት እውነተኛ፥ ብርታት ያለውና የተለወጠ ሕይወትን የሚያስገኝ ነው።

ያዕቆብ ይህንን እውነተኛ የሚያድን እምነት ያብራራል። በመጀመሪያ ይህ እምነት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ ነው። መንፈሳዊ ልደታችንን የተቀበልነው በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ነው (ያዕ. 1፡18)። ቃሉን እንቀበላለን፤ ይህም ደኅንነትን ይሰጠናል (ያዕ. 1፡21)። «እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው፥ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» (ሮሜ 10፡17)። ያዕቆብ አብርሃምንና ረዓብን ይህንን እምነት ለመግለጫነት ይጠቀምባቸዋል። ምክንያቱም ሁለቱም የእግዚአብሔርን መልእክት በመስማት የተቀበሉ ነበሩ።

እምነት መልካም የሚሆነው ከምናምንበት ጉዳይ አንፃር ነው። እግዚአብሔርን የማያውቅ ሰው በድንጋይ በተቀረጸው ምስል ፊት ይሰግዳል፤ ይረዳውም ዘንድ በዚያ ምስል ላይ ይደገፋል፤ ነገር ግን እንዳችም እርዳታ አያገኝም። የምናምነው በትክክለኛ ነገር እስካልሆነ

ድረስ፥ የእምነታችን ትልቅነት ዋጋ የለውም። «አምናለሁ» የሚለው ቃል የብዙ እውነተኛና ቅን ሰዎች ምስክርነት ሊሆን ይችላል። ትልቁ ጥያቄ ግን «እምነትህ በማን ላይ ነው? የምታምነውስ ምንድን ነው?» የሚል ነው። ደኅንነትን ያገኘው እምነትን በማመን አይደለም። ነገር ግን በቃሉ በተገለጠው በክርስቶስ በማመን ነው።

ኃይል ያለው እምነት የተመሠረተው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ነው። ይህ እምነት ሙሉውን ሰው የሚያካትት ነው። የሞተ እምነት የሚነካው እውቀትን ብቻ ነው። የአጋንንት ዓይነት እምነት ደግሞ አእምሮንና ስሜትን የሚነካ ነው። ኃይል ያለው እምነት ግን ፈቃድን ያካትታል። በእውነተኛው የሚያድን እምነት ውስጥ ሰው በሁለንተናው ተሳትፎ አለው። አእምሮ እውነትን ይረዳል፤ ልብ እውነትን ይፈልጋል፤ ፈቃድ ደግሞ በዚህ እውነት ላይ ይሠራል። በዕብ. 11 የተገለጡት የእምነት ሰዎች የተግባር ሰዎች ነበሩ። እግዚአብሔር ለተናገራቸው የታዘዙ ሰዎች ነበሩ። እንደገና ለመጥቀስ «እምነት ያለመረጃ ነገርን ማመን አይደለም፤ እምነት የሚያስከትለው ነገር ምንም ቢሆን መታዘዝን መቻል ማለት ነው።»

እውነተኛ የሚያድን እምነት ወደ ተግባር ይመራል። ኃይል ያለው እምነት በእውቀት የሚገኝ ጥልቅ ምርምር ወይም ስሜታዊ ውዥንብር አይደለም፤ በፈቃድ ላይ ወደ ተመሠረተ መታዘዝ የሚመራ ነው። ይህ መታዘዝ ደግሞ የአንድ ጊዜ ተግባር ብቻ ሳይሆን በሕይወት ዘመን ሁሉ የሚቀጥል ነው፤ ወደ ተግባር የሚመራ ነው።

በአዲስ ኪዳን በርካታ የተለያዩ ተግባራት ተጠቅሰዋል። «የሕግ ሥራዎች» (ገላ. 2:16) አንድ ኃጢአተኛ የሙሴን ሕግ በመጠበቅ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የሚያደርገውን ሙከራ ያሳያል። በእርግጥ አንድ ኃጢአተኛ በሕግ ሥራዎች ለመዳን አይችልም፥ «የሥጋ ሥራዎች»ን የሚፈጽሙት (ገላ. 5:19) ለአሮጌው ተፈጥሮአቸው የሚኖሩ ያልዳኑ ሰዎች ነው። በተጨማሪ «ክፉ ሥራዎች» (ቆላ. 1:21) ና «የሞቱ ሥራዎች» (ዕብ. 9:14) የሚባሉ ነገሮች አሉ። ኃይል ያለው የሚያድን እምነት ባለበት ቦታ ሁሉ ምን ጊዜም ቢሆን መልካም ሥራዎችን ታገኛለህ።

ያዕቆብ በመቀጠል ይህንን መሠረታዊ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በታወቁ ሁለት ሰዎች ሕይወት ምሳሌነት ያብራራዋል፤ እነርሱም:- አብርሃምና ረዓብ ናቸው። እነዚህ ሁለት ሰዎች በጣም የተለያዩ ሰዎች ናቸው። አብርሃም አይሁዳዊ ሲሆን ረዓብ ደግሞ

ከአሕዛብ ወገን ነበረች። አብርሃም የእግዚአብሔር ሰው ሲሆን ረዓብ ደግሞ አመንዝራ ሴት ነበረች። አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበረ፤ ረዓብ ከእግዚአብሔር ጠላቶች ወገን ነበረች። ምንም እንኳ የጋራ የሆነ ነገር ባይኖራቸውም ሁለቱም የሚያድን እምነት ነበራቸው።

ለዚህ መግለጫ የሚሆን መሠረታዊ እውነታ ለማግኘት ዘፍ. 15 ና 22 ማንበብ ይኖርብህ ይሆናል። እግዚአብሔር አብርሃምን ከከለዳውያን ዑር አውጥቶ በእርሱ አማካይነት ታላቁን የእስራኤልን ሕዝብ ይመሠርት ዘንድ ወደ ከነዓን መራው። እግዚአብሔር አዳኙ ኢየሱስን ወደ ዓለም ለመላክ የተጠቀመው በዚህ ሕዝብ ነው። የአብርሃምም የደኅንነት ልምምድ በዘፍ. 15 ተመዝግቦ እናገኘዋለን። እግዚአብሔር ለባሪያው ለአብርሃም የምሽት ከዋክብትን አሳየውና ቃል ኪዳን ገባለት። «ዘርህም እንደዚሁ ይሆናል አለው።» ለዚህ የተሰፋ ቃል አብርሃም የሰጠው ምላሽ ምን ነበር? «አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት» (ዘፍ. 15፡5-6)።

ተቆጠረለት የሚለው ቃል ሕጋዊ የሆነ የሒሳብ ቃል ነው። ትርጉሙም «በአንድ ሰው አሳብ ውስጥ ተመዘገበ ማለት ነው» እንደ ኃጢአተኛነቱ የአብርሃም መንፈሳዊ የባንክ ደብተር ባዶ ነበር። ደሀ ነበር፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ስላመነ እግዚአብሔር በአብርሃም መዝገብ ላይ «ጻድቅ» ብሎ ጻፈበት። ለዚህ ጽድቅ አብርሃም የሠራው ሥራ የለም፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ በስጦታ መልክ ተቀበለው። በእምነት ጻድቅ ተብሎ ተጠራ፤ በእምነት ጸደቀ (ሮሜ 4ን አንብብ)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጽድቅ እጅግ ጠቃሚና መሠረታዊ ትምህርት ነው። ጽድቅ እግዚአብሔር አንድ ያመነ ኃጢአተኛን ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ሥራ ምክንያት ጻድቅ ብሎ የሚጠራበት የእርሱ የራሱ ሥራ ነው። ይህ ተግባር የአንድ ጊዜ ቅፅበታዊ ሥራ እንጂ የሂደት ውጤት አይደለም። አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ እግዚአብሔር ለእርሱ የሚሠራው ሥራ እንጂ ኃጢአተኛው የሚሠራው ሥራ አይደለም። ደግሞ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚፈጸም የማይለወጥ ተግባር ነው።

ይህ ተግባር በኃጢአተኛና በእግዚአብሔር መካከል በግል የሚፈጸም ውል ከሆነ አንድ ሰው ጻድቅ መሆኑን እንዴት መናገር እንችላለን? የአብርሃም ምሳሌነት የዚህ ጠቃሚ ጥያቄ መልስ ይሆናል፡- ጻድቁ ሰው የተለወጠ ሕይወት ይኖረዋል፤ እግዚአብሔርን ይታዘዛል፤ እምነቱ ደግሞ በሚሠራው ሥራ ይገለጣል።

ያዕቆብ በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ስለ ተፈጸመ ሌላ ጉዳይ ይናገራል። ይህ ጉዳይ አብርሃም ከተለወጠ ከብዙ ዓመት በኋላ የተፈጸመ ነው። ይስሐቅን መሥዋዕት አድርጎ እንዲያቀርብ እግዚአብሔር አዝዞት ነበር (ዘፍ. 22)። አብርሃም የዳነው አስቸጋሪ የሆነውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመፈጸም አይደለም። በመታዘዙ የዳነ ሰው መሆኑን የሚያሳይ ነው። «እምነትን ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደነበር፥ በሥራውም እምነት እንደተፈጸመ ትመለከታለህን?» (2:22)። በእምነትና በሥራ መካከል የጠበቀ ግንኙነት አለ። አንድ ሰው እንደገለጸው «አብርሃምም የዳነው በእምነትና በሥራ አይደለም፥ ነገር ግን በሚሠራ እምነት እንጂ።»

አብርሃም የጸደቀው በእምነት እስከሆነ ድረስ (ሮሜ 4 ተመልከት) እንዴት በሥራ ሊጸድቅ ይችላል? (2:21)። «በእምነት በእግዚአብሔር ፊት ጸደቀ»። በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆኑም ታወጀ። በሥራ በሰዎች ፊት ጸደቀ። ጻድቅ መሆኑ በሚሠራው ሥራ ታየ። በእርግጥ አብርሃም ልጁን በመሠዊያ ላይ ባደረገ ጊዜ ያየው ሰው የለም፤ ነገር ግን በዘፍ. 22 በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት የተመዘገበው ታሪክ በሥራ የተገለጠውን የአብርሃምን እምነት አሳየ።

ዲ.ኤል. ሙዲ ብዙ ጊዜ እንዲህ ይል ነበር፡- «እያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ጫማ መጫማት አለበት!» ይህንን ያለው የተዋጣለት ጫማ ነጋዴ ስለ ነበረ አይደለም፤ ይህን ያለው ራሱን ለጌታ የሰጠ ክርስቲያን ስለነበረ ነው። ኃይል ያለው እምነት እግዚአብሔርን በመታዘዝ በዕለታዊ ሕይወትና ተግባር እራሱን ይገልጣል። ሐዋርያው ጳውሎስ በቲቶ መልእክቱ «እግዚአብሔርን እንዲያውቁ በግልጥ ይናገራሉ ዳሩ ግን ... በሥራቸው ይክዱታል» (ቲቶ 1:16)። ዛሬም ቢሆን ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባሎች ሕይወት ይህንን ያሳያል አለ ጳውሎስ። በተጨማሪም እንዲህ በማለት ጽፏል፡- «እግዚአብሔርንም የሚያምኑት በመልካም ሥራ በጥንቃቄ እንዲጸኑ፥ እነዚህን አስረግጠህ እንድትናገር እፈቅዳለሁ» (ቲቶ 3:8)።

ያዕቆብ በሁለተኛ ደረጃ በምሳሌነት ያቀረባት ረዓብ ናት፤ ታሪኳን በኢያሱ 2 ና 6 እናገኘዋለን። እስራኤላውያን የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ የኢያሪኮን ከተማ እየከበቡ ነበሩ። ኢያሱ ሰላዮችን ወደ ምድሪቱ በላከ ጊዜ ጋለሞታይቱ ረዓብን አገኙአት። ይህች ሴት ሰላዮቹን ከአደጋ በመጠበቅ እግዚአብሔር የተናገረውንና ሊያደርግ ያለውን እንደምታምን ነገረቻቸው። ሰላዮቹም እግዚአብሔር ምድሪቱን

በሚሰጣቸው ጊዜ እርሷንና ቤተሰቧን እንደሚያድኑ ቃል ገቡላት፤ እንዳሉትም አደረጉ።

ግሩም ታሪክ ነው። ደግሞም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚያድን እምነት ከቀረቡ ታላላቅ ምሳሌዎች አንዱ ነው (ዕብ. 11፡31)። ረዓብ ቃሉን ሰማችና የምትኖርባት ከተማ እንደተፈረደባት አወቀች። ይህ እውነት እርሷንም ሆነ በከተማይቱ የነበሩትን ሰዎች ልብ አቀለጠ (ኢያሱ 2፡11)። ረዓብ በአእምሮዋና በስሜቷ ብቻ ሳይሆን በፈቃዷም ምላሽን በመስጠት ስለ ጉዳዩ አንድ ነገር አደረገች። የአይሁድ ሰላዮችን ሕይወት ከአደጋ ለመጠበቅ የራሷን ሕይወት አደጋ ላይ ጣለች፤ በተጨማሪ ነፃ የመውጣታቸውን መልካም ምሥራች ለቤተሰቧ በማካፈል ሕይወቷን አደጋ ላይ ጣለች። በኢያሱ 2 ላይ ጋለሞታ ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጡ ቃል ከዚህ የሰፋ ትርጉም አለው «የእንግዶች ማደሪያ አስተናጋጅ» እንደማለትም ይሆናል። ረዓብ የእንግዳ ማስተናገጃ የነበረው ሆቴል ስለነበራት ሰላዮች ወደዚህ መምጣታቸው የተለመደ ነበር። በያዕቆብ 2፡25 የተጠቀሰው «ጋለሞታይቱ» የሚለው ቃል ግን መጥፎ ሥነ-ምግባር የነበራት ሴት እንደነበረች የሚያሳይ ነው። በዕብራውያን 11፡31 ላይም የተጠቀሰው የዚሁ ተመሳሳይ ነው። ማቴ. 1፡5 ደግሞ አስራኤላዊን እንዳገባችና የጌታችን የዘር ግንድ እንደነበረች ያመለክታል። ምን ዓይነት አስደናቂ ጸጋ ነው! በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱ የመጀመሪያ ነፍሳት ማራኪዎች አንዷ ሆና በዮሐ. 4 ከተጠቀሰችው ሳምራዊት ሴት ጋር የምትወዳደር ሆነች።

ረዓብ የሞተ ዓይነት እምነት ማለት የእውቀት እምነት ብቻ ሊኖራት ይችል ነበር። ወይም የአጋንንት ዓይነት ማለት አእምሮአዊና ስሜታዊ እምነት ሊኖራት ይችል ነበር፤ በእውቀት ሊበራና ስሜቷ ሊንቀሳቀስ ይችል ነበር። ነገር ግን ኃይል ያለው እምነት ተለማመደች። አእምሮዋ እውነትን አወቀ፤ ልቧ በእውነት ተነቃቃ፤ ፈቃዷ ደግሞ በእውነት ላይ ተግባርን በመፈጸም ተገለጠ። እምነቷን በሥራዋ ገለጠች።

ረዓብ ስለ ጉዳዩ የነበራትን እጅግ አነስተኛ መረጃ ስታስብ እምነቷ እንዴት አስደናቂና እውነተኛ እንደነበር ትገነዘባለህ። ዛሬ በቃሉና በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ አማካይነት ስለ እግዚአብሔር ሙሉ መገለጥ አለን። በኃጢአታችን ሊወቅሰንና ሊያስተምረን መንፈስ ቅዱስ አለን። «ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል» (ሉቃስ 12፡48)። የረዓብ እምነት ኃጢአተኞችን የሚወቅስና የሚከስስ የጽሑፍ መረጃ ሆኖአል።

በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰለ ክርስቲያን እውነትን እንደሚለማመድ ያዕቆብ ምዕራፍ 2 አጠንክሮ ይናገራል። እውነተኛ መሠረታዊ ትምህርቶችን ይዞ የሚቀመጥ ብቻ ሳይሆን፥ መሠረታዊ ትምህርቶችን በዕለታዊ ሕይወቱ ይለማመዳቸዋል። እምነቱ አዋቂ ነን ባዮች የሚኖራቸው የሞተ እምነት ወይም የወደቁት መናፍስት ያላቸው የአጋንንት ዓይነት እምነት አይደለም። ሕይወትን የሚለውጥና ለእግዚአብሔር የሚሠራ እንደ አብርሃምና ረዓብ ዓይነት ኃይል ያለው እምነት ነው።

እያንዳንዱ ክርስቲያን የራሱን ልብና ሕይወት ሊመረምርና እውነተኛ ኃይል ያለውን የሚያድን እምነት ባለቤት መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። «በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ» (2ኛ ቆሮ. 13፡5)። ሰይጣን እጅግ የረቀቀ አታላይ ነው። አንዱ ግታለያው ማስመሰል ነው። እምነትን በሚመስል ነገር ግን ምንም ከእምነት ጋር ግንኙነት በሌለው ነገር አንድን ሰው ማታለል ከቻለ ያንን ሰው በቁጥጥሩ ሥር ይዞአል ማለት ነው።

እራሳችንን በምንመረምርበት ጊዜ ልንጠይቃቸው የሚገቡ አንዳንድ ጥያቄዎች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል፡-

1. ኃጢአተኛነቴን በእውነትና በቅንነት ተቀብየአለሁን? ይህንንም ለራሴና ለጌታ የተናገርኩበት ጊዜ ነበርን?
2. ሊመጣ ካለው ቁጣ እንድሸሽ ልቤ የተነሣሣበት ጊዜ ነበርን? በኃጢአቴ በእርግጥ ያዘንኩበት ጊዜ ነበርን?
3. ክርስቶስ ለእኔ ኅጢአት እንደሞተና ከሞት እንደተነሣ የሚናገረው ወንጌል በእርግጥ ገብቶኛልን? እራሴን ማዳን እንደማልችል ተረድቼ አምኜአለሁን?
4. በኃጢአቴ በእውነት ንስሐ ገብቼ ኃጢአቴን ትቼአለሁን? ወይስ ኃጢአትን በምሥጢር እየወደድኩ በኃጢአት ደስ እሰኛለሁ? ወይስ ኃጢአትን እየጠላሁ እግዚአብሔርን እፈራለሁ?
5. ለደኅንነቴ የታመንኩት በክርስቶስ ብቻ ነውን? በቃሉና በመንፈሱ አማካይነት ከእርሱ ጋር በማደርገው ሕያው ግንኙነት ደስተኛ ነኝን?
6. በሕይወቴ ለውጥ ነበርን? መልካም ሥራዎችን ያለማቋረጥ እሠራለሁ፥ ወይስ መልካም ሥራዎቼ አልፎ አልፎ የሚደረጉና ደካማ ናቸው? የጌታ በሆኑ ነገሮች ለማደግ እፈልጋለሁን? ሌሎች ሰዎች ከኢየሱስ ጋር ስለመሆኔ ሊመሰክሩ ይችላሉን?

7. ክርስቶስን ለሌሎች ለማካፈል እፈልጋለሁን? ወይስ በእርሱ አፍራለሁ?

8. ከእግዚአብሔር ሕዝቦች ጋር በሚደረግ ኅብረት ደስ እሰኛለሁን? አምልኮ ደስ ያሰኘኛልን?

9. ለጌታ መመለስ ዝግጁ ነኝን? ወይስ በሚመጣበት ጊዜ አፍራለሁ?

እያንዳንዱ ክርስቲያን አንድ ዓይነት የእምነት አቋም እንደሌለው እርግጥ ነው። የቅድስና ደረጃዎቹም ይለያያሉ። በአብዛኛው ግን ከላይ የተዘረዘሩት መንፈሳዊና እራስን የመመርመሪያ ጥያቄዎች አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ያለውን እውነተኛ መንፈሳዊ አቋም ለመወሰን ይረዳሉ።

«አቤቱ፥ መርምረኝ ልቤንም እወቅ፤ ፈትነኝ መንገዴንም እወቅ፤ በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ፤ የዘላለምንም መንገድ ምራኝ» (መዝ. [139]፡23 ና 24)።

ያዕቆብ 3፡1-12

«ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ፥ የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁና። ሁላችን በብዙ ነገር እንሰናከላለንና፤ በቃል የማይሰናከል ግንም ቢኖር እርሱ ሥጋውን ሁሉ ደግሞ ሊገታ የሚችል ፍጹም ሰው ነው። እነሆ፥ ፈረሶች ይታዘዙልን ዘንድ ልጓም በአፋቸው ውስጥ እናገባለን፥ ሥጋቸውንም ሁሉ እንመራለን። እነሆ፥ መርከቦች ደግሞ ይህን ያህል ታላቅ ቢሆኑ በዐውሎ ነፋስም ቢነዱ፥ የመሪ ፈቃድ ወደሚወደው ስፍራ እጅግ ታናሽ በሆነ መቅዘፊያ ይመራሉ። እንዲሁም አንደበት ደግሞ ትንሽ ብልት ሆኖ በታላላቅ ነገር ይመካል። እነሆ፥ ትንሽ እሳት እንዴት ያለ ታላቅ ጫካ ያቃጥላል።

«አንደበትም እሳት ነው። አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ዓለም ሆኖአል፤ ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና፥ የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል፥ በገሃነምም ይቃጠላል። የአራዊትና የወፎች የተንቀሳቃሾችና በባሕር ያለ የፍጥረት ወገን ሁሉ በሰው ይገራል፥ ደግሞ ተገርቶአል፤ ነገር ግን አንደበትን ሊገራ ማንም ሰው አይችልም፤ የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፋት ነው። በእርሱ ጌታና አብን እንባርካለን፤ በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማለን፤ ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ። ወንድሞቼ ሆይ፥ ይህ እንዲህ ሊሆን አይገባም። ምንጭስ ከአንድ አፍ የሚጣፍጥና የሚመርን ውኃ ያመነጫልን? ወንድሞቼ ሆይ፥ በለስ ወይራን ወይስ ወይን በለስን ልታፈራ ትችላለችን? ከጨው ውኃም ጣፋጭ ውኃ አይወጣም።»

በዓለም ላይ አነስተኛ ሆና ከፍተኛ ችግርን የምትፈጥር ነገር

በምዕራፍ 1 ና 2 ላይ ያዕቆብ የበሰለ ክርስቲያን ባሕርያት ስለሆኑ ሁለት ነገሮች ገልጾአል። እነርሱም በመከራ መታገስ (ምዕራፍ 1) ና እውነትን መለማመድ (ምዕራፍ 2) ናቸው። በዚህ በሦስተኛው ምዕራፍ ደግሞ የበሰለ ክርስቲያን ሦስተኛ ባሕርይ ስለሆነው ነገር ይናገራል፤ ይህም፡- አንደበቱን ለመግታት መቻሉ ነው።

አንድ ጊዜ አንድ በመጋቢነት አገልግሎት ላይ የተሰማራ ጓደኛዬ የቤተ ክርስቲያኑ አባል ስለሆነች አንዲት ሐሜተኛ ሴት አጫውቶኛል። አብዛኛውን ጊዜዋን የምታሳልፈው ሊሰማት ለሚችል ለማንኛውም ሰው በስልክ ሐሜትን እያወራች ነበር።

አንድ ቀን ወደዚህ መጋቢ ትመጣና፡- «እግዚአብሔር ስለ ሐሜት ኃጢአት ወቅሶኛል፤ አንደበቴ እራሴንና ሌሎችን ችግር ውስጥ እየከተተ ነው» አለችው።

ይህ መጋቢ የሆነ ጓደኛዬ ግን ይህንን ነገር ከዚህ በፊት ደጋግማ ታደርገውና ተጸጽቻለሁ እያለችም ትመለስበት ስለነበር ከልቧ እንዳልሆነ ተረድቶ ነበር። ስለዚህ፡- «ጥሩ ነው፤ ታዲያ ምን ለማድረግ አሰበሻል?» አላት።

እርሷም መልሳ ጥልቅ በሆነ የእውነተኛነት ስሜት «አንደበቴን በመሠዊያው ላይ ማድረግ እፈልጋለሁ አለችው።

መጋቢው ጓደኛዬም በዝግታ፡- «ለምላስሽ የሚበቃ ትልቅ መሠዊያ የለም» በማለት በነገሩ እንድታስብበት ተዋት።

ያዕቆብ መልእክቱን የሚጽፍላቸው ክርስቲያኖች በአንደበታቸው ከፍተኛ ችግር የነበረባቸው እንደሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህ ያዕቆብ አስጠንቅቆአቸው ነበር። «ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፤ ለመናገርም የዘገየ ለቁጣም የዘገየ ይሁን» (ያዕ. 1፡19)። አንደበቱን የማይገታ አማኝ አምልኮ ከንቱ ነው (ያዕ. 1፡26)። ንግግራችንም ሆነ ተግባራችን ልክ በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንዳለን ቆጥረን የምናደርገው መሆን አለበት (ያዕ. 2፡12)። ያዕ. 4፡19፤ 4፡11-12 ና የመሳሰሉትን

ከፍሎች ስታነብብ ይህ ጉባኤ አንዳንድ አስደናቂ ስብሰባዎች እንደነበሩት መገመት ይቻላል።

የንግግር ኃይል እግዚአብሔር ከሰጠን ታላላቅ ኃይላት አንዱ ነው። በአንደበቱ እግዚአብሔርን ሊያመሰግን፥ ሊጸልይ፥ ቃሉን ሊሰብክና የጠፉትን ወደ ክርስቶስ ሊመራ ይችላል። ይህ አስደናቂ ዕድል ነው። ነገር ግን በዚያው አንደበት ሰው ውሸትን በመናገር ምስክርነቱን ሊያበላሽ፥ ወይም የሰውን ልብ ሊያሳዝን ይችላል። የንግግርን ችሎታ በሚገባ ከተጠቀምንበት በሌሎች ላይ በጎ ተጽዕኖ በማድረግ ከፍተኛ ውጤት የሚያስገኝ ችሎታ ነው፤ እኛ ግን ይህንን ችሎታ እንደሚገባ አንጠቀምበትም።

የተገታ አንደበት አስፈላጊነትና ንግግራችን ሊያስከትላቸው ስለሚችላቸው ከፍተኛ ውጤቶች ለመግለጽ ያዕቆብ ስድስት መግለጫዎችን አቅርቧል። እነዚህም፡- ልጓም፥ መቅዘፊያ፥ እሳት፥ የተመረዘ እንስሳ፥ ምንጭና የበለስ ዛፍ ናቸው። እነዚህ ስድስት መግለጫዎች የአንደበትን ሦስት ኃይላት በሚገልጹ ሦስት ትርጉም ሰጪ መንገዶች ልንከፋፍላቸው እንችላለን።

የመምራት ኃይል፡- ልጓምና መቅዘፊያ (3፡1-4)

በጉባኤው የነበሩ ሰዎች በሙሉ አስተማሪና መንፈሳዊ መሪ ለመሆን ፈልገው እንደነበር ግልጽ ነው። ስለዚህም ያዕቆብ «ወንድሞች ሆይ፥ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ» በማለት አስጠነቀቃቸው (ያዕ. 3፡1)። ብዙዎች ይህንን የአገልግሎት ስፍራ የፈለጉት ስፍራው በነበረው ሥልጣንና መብት ሳይሆን አልቀረም፤ ከፍተኛ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዳለበት ግን ዘንግተው ነበር። ቃሉን የሚያስተምሩ ሰዎች የሚቀበሉት ፍርድ ከሌሎች የባሰ ነው። አስተማሪዎች አንደበታቸው ሊጠቀሙበት የሚገባው የእግዚአብሔርን እውነት ለሌሎች በማካፈል ነው። በአንደበት ኃጢአትን መሥራት ደግሞ ቀላል ነው። በተጨማሪ አስተማሪዎች የሚያስተምሩትን ነገር ሊኖሩበት ይገባል፤ ያለበለዚያ ግን ግብዝነት ነው። ያልተዘጋጀ ወይም መንፈሳዊ ሕይወቱ ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር የማይጣጣም አስተማሪ ሊያስከትለው የሚችለውን ጉዳት ማሰብ ትችላለህ።

በኃጢአት የሚፈተኑና ኃጢአትን የሚያደርጉ ግን አስተማሪዎች ብቻ አይደሉም። እያንዳንዱ ክርስቲያን «ሁላችንም በብዙ ነገር እንሰናከላለን» (ያዕ. 3፡2) የሚለው ቃል እውነት መሆኑን አምኖ

መቀበል አለበት። ከኃጢአት ሁሉ ደግሞ በአንደበት የሚሠራ ኃጢአት ቅድሚያ አለው። አንደበቱን መግታት የቻለ ሰው በአጠቃላይ ሰውነቱን መቆጣጠር እንደሚችል ያረጋገጠ ሰው ነው። የበሰለ ፍጹም ሰው ለመሆኑ ማረጋገጫ አቅርቦአል ማለት ነው።

ያዕቆብ በአንደበት የሚፈጸም ኃጢአትን በአጠቃላይ በሌላው ሰውነት ከሚፈጸም ኃጢአት ጋር በማያያዙ ስሕተትን አድርጎአልን? አላደረገም። ምክንያቱም ንግግሮች ብዙ ጊዜ የሚያመሩት ወደ ተግባር ነው። በ2ኛው የዓለም ጦርነት «ያልተገታ አንደበት መርከብን ያሰጥማል!» የሚሉ የግድግዳ ጽሑፎች ማየት በጣም የተለመደ ሆኖ ነበር። በተጨማሪ ያልተገታ አንደበት ሕይወትን ያጠፋል። አንድ ሰው ጥንቃቄ የጎደለው አንድ ዐረፍተ-ነገር ከአንደበቱ ከወጣ በኋላ ወዲያውኑ እራሱን በጠብ ውስጥ ያገኘዋል። ከአንደበቱ የቀሩት የሰውነቱን ክፍሎች በሙሉ ለመከላከያ እንዲቆሙ ያስገድዳቸዋል።

ያዕቆብ ልጓምንና መቅዘፊያን ለመግለጫነት አቅርቦአል። እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ትናንሾች ነገሮች ናቸው፤ ነገር ግን ልክ እንደ አንደበት ተግባራቸው ኃይለኛ ነው። ትንሽ ልጓም ኃይለኛውን ፈረስ ለመቆጣጠር ታስችላለች። ትንሽ መቅዘፊያም ቀዛፊውን የትልቁን መርከብ አቅጣጫ ወደሚፈልገው እንዲያስኬድ ያስችለዋል። አንደበት በአካላችን ውስጥ ትንሿ አካል ስትሆን ታላላቅ ነገሮችን የማድረግ ኃይል ግን አላት።

ልጓምም ሆነ መቅዘፊያ ተግባራቸው የሚካሄደው ተቃራኒ ኃይላትን በማሸነፍ ነው። ልጓም የፈረስን እንስሳዊ ተፈጥሮን ማሸነፍ አለበት፤ መቅዘፊያ ደግሞ መርከቡ ወዳልፈለገው አቅጣጫ እንዲሄድ የሚታገሉትን ነፋስንና ሌሎች ነገሮችን ማሸነፍ መቻል አለበት። የሰው አንደበትም ተቃራኒ ኃይላትን ማሸነፍ አለበት። እኛን ሊቆጣጠረንና ኃጢአት እንድንፈጽም ሊያደርገን የሚሻ አሮጌ ተፈጥሮ አለን። መናገር የሌለብንን ነገር እንድንናገር የሚያደርጉ ሁኔታዎች በዙሪያችን አሉ። በውስጣችን ያለው የኃጢአት ተፈጥሮና ከውጭ የሚያጋጥመን ግፊት አንደበታችንን ሊቆጣጠሩት ይፈልጋሉ።

ልጓምም ሆነ መቅዘፊያ በሚገባ ሥራቸውን እንዲሠሩ በጠንካራ እጆች ሥር መሆን አለባቸው። ባለሙያ ፈረሰኛ የፈረሱን ጉልበት ከፍተኛ ኃይል በቁጥጥሩ ሥር ያደርገዋል። ደግሞም ልምድ ያለው ቀዛፊ መርከቡን በከፍተኛ ማዕበል ውስጥ እንኳ በድፍረት ይነዳዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ አንደበትን በሚቆጣጠርበት ጊዜ የተሳሳቱ ነገሮችን እንናገራለን ብለን ጨርሶ መፍራት አያስፈልገንም ወይም ትክክለኛ ነገሮችን በተሳሳተ

መንገድ እንናገራለን ብለን መፍራት አያስፈልግም። ጠቢቡ ሰለሞን ሲያስጠነቅቅ «ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው» አለ (ምሳሌ 18፡21)። ዳዊትም እንዲህ ብሎ መጸለዩ የሚያስደንቅ አይሆንም፡- «አቤቱ፥ ለአፌ ጠባቂ አኑር፥ የከንፈሮቼን መዝጊያ ጠብቅ። ልቤን ወደ ክፉ ነገር አትመልሰው፥ ዓመፃን ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር ለኃጢአት ምክንያት እንዳልሰጥ» (መዝ. [141]፡3-4)። ዳዊት ለትክክለኛ ንግግር መሠረቱ ልብ መሆኑን ተረድቶ ነበር። «በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና» (ማቴ. 12፡34)። ኢየሱስ ክርስቶስ የልብ ጌታ ሲሆን የከናፍርታችንም ጌታ ይሆናል።

ልጓምና መቅዘፊያ የመምራት ኃይል አላቸው ማለት በሌሎች ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ያደርጋሉ ማለት ነው። የደነበረ ፈረስ ለጋላቢው፥ ወይም የተሰባበረና መስጠም የጀመረ መርከብ ደግሞ ለተሳፋሪዎች የተለያዩ ጉዳት ወይም ሞትን ሊያስከትሉ ይችላሉ። የምንናገራቸው ቃላቶችም በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ ጉዳት ያመጣሉ። አንድ ዳኛ ፍርድ ቤት ተከሰሶ በቀረበ ሰው ላይ ጥፋተኛ ነህ ወይም አይደለህም ብሎ የሚያስተላልፈው ቃል የተከሰሰውን ሰው፥ የቤተሰቡንና የጓደኞቹን ሕይወት ሁሉ የሚነካ ነው። የአሜሪካን ወይም የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንቶች የሚናገሩት ጥቂት ቃሎችና የሚፈርሙአቸው የተወሰኑ ወረቀቶች ሕዝቡን ወደ ጦርነት የሚከትቱ ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ ወላጅ ለልጁ የሚሰጠው ቀላል የ«አዎን» ወይም የ«አይደለም» መልስ እንኳ የአንድን ልጅ የሕይወት አቅጣጫ በከፍተኛ ሁኔታ ሊነካ ይችላል።

በምትናገራቸው ወይም ሳትናገር በምትተዋቸው ቃላቶች ምክንያት ልትሰጥ የምትችለውን ምሪት አሳንሰህ ማየት ጨርሶ አይገባም። ኢየሱስ በውኃ ጉድጓድ አጠገብ ላገኛት ሴት የተናገራት ቃል በእርሷና በጎረቤቶችዋ ሕይወት ተአምራዊ የሆነ ለውጥ ተፈጸመ (ዮሐ. 4)። ጴጥሮስ በጰንጠቆስጤ ቀን (በበዓለ ኃምሳ) በሰበከው ስብከት 3000 የሚያህሉ ነፍሳት በክርስቶስ በማመን ወደሚገኝ ደኅንነት መጡ (የሐዋ. 2)።

በሚያዝያ 21/1855 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ኤድዋርድ ኪምቦል የተባለ ሰው ቦስተን የሚገኝ መሸጫ መደብር በመሄድ ወጣቱን ዲ.ኤል. ሙዲን ወደ ክርስቶስ መራው። ውጤቱም በታሪክ ውስጥ እጅግ ታላቅ የሚባል ወንጌላዊን ማፍራት ሆነ። የዚህ ሰው አገልግሎት እስካሁን ድረስ

ቀጥሎ አል። አንደበት ሌሎችን ትክክለኛ ወደሆኑ ምርጫዎች የመምራት ኃይል አለው።

መጽሐፈ ምሳሌ በተደጋጋሚ በማንበብ ስለ ንግግር የተጠቀሱ በርካታ ጥቅሶችን መመልከት እጅግ ጠቃሚ ነው። «የለዘበች ምላስ ቁጣን ትመልሳለች፤ ሸካራ ቃል ግን ቁጣን ታስነሣለች» (ምሳሌ 15፡1)። «ውሸተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው» (ምሳሌ 12፡22)። «በቃል ብዛት ውስጥ ኃጢአት ሳይኖር አይቀርም፤ ከንፈሩን የሚገታ ግን አስተዋይ ነው» (ምሳሌ 10፡19)። አዎን አንደበት እንደ ልጓምና መቅዘፊያ ነው፤ የመምራት ኃይል አለው። አንደበታችን ሰዎችን ወደ ትክክለኛ መንገድ መምራቱ እጅግ አስፈላጊ ነው!

የመደምሰስ ኃይል፡- እሳትና የተመረዘ እንስሳ (3፡5-8)

በለንደን በአንድ መስቀለኛ መንገድ ላይ የሚገኘውን አሮጌ የመጻሕፍት መደብር እየጎበኘሁ ነበር። የመጻሕፍት መደብሩ የጠበቅኩትን ያህል ከፍተኛ አይደለም ባልኩት ጊዜ ሠራተኛው እንዲህ ብሎ መለሰልኝ፡- «በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በአንድ ምሽት ተስፈንጣሪ ቦምቦች ቤተ መጻሕፍቱን በመምታታቸው ቢያንስ አንድ ሚሊዮን መጻሕፍት ወድመዋል!» አለኝ።

በሌላ ጊዜ አንድ ጓደኛችን እኔና ባለቤቴን በካሊፎርኒያ ወደሚገኝ እጅግ ውብ ወደሆነ ጫካ ለሽርሽር ይዞን ሄደ። በእሳት እጅግ ወደ ወደመ አንድ አካባቢ ደረስን። በዚህ እሳት በደረሰ ጥፋት ምክንያት የተፈጥሮ ገጽታ መበላሸቱ ብቻ ሳይሆን በብዙ ሚሊዮን ብር የሚቆጠር ንብረትም ወድሞአል። እየተዘዋወርን እያለ ይህ ሁሉ ጥፋት የደረሰው አንድ ሰው በለኮሰው ሲጋራ መሆኑን ጓደኛዬ አጫወተኝ።

እሳት ከትንሽ ብልጭታ ሊጀምር የሚችል ሲሆን ከተማን እስኪያጠፋ ድረስ ለማደግ ይችላል። በቺካጎ ኦሊሪ በተባለ መጋዘን በጥቅምት 8/1871 እ.ኤ.አ. ከምሽቱ 2፡30 የጀመረ እሳት እጅግ ለመስፋፋት በመቻሉ ከመቶ ሺህ የሚበልጡ ሰዎችን ያለ መጠጊያ አስቀረ፤ አሥራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሕንጻዎች ተደመሰሱ፤ ሦስት መቶ የሚያህሉ ሰዎች ሞቱ። በዚህ አደጋ ከተማይቱ አራት መቶ ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር የሚገመት ጉዳት ደረሰባት።

ከአንደበታችን የሚወጡ ቃላት እሳትን ሊያስነሡ ይችላሉ። «እንጨት ባለቀ ጊዜ እሳት ይጠፋል፤ ጆሮ ጠቢ በሌለበትም

ዘንድ ጠብ ጸጥ ይላል። ከሰል ፍምን እንጨትም እሳትን እንዲያበዛ፥ እንዲሁ ቁጡ ሰው ጠብን ያበዛል» (ምሳሌ 26:20፥21)። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አንደበታቸውን ሊቆጣጠሩ የማይችሉ አባላት ወይም በኃላፊነት ስፍራ ያሉ ሰዎች ይገኛሉ፤ የእነርሱ መኖር ውጤት ጥፋት ነው። ትተው እንዲወጡ ወይም የኃላፊነት ስፍራቸው በሌላ ሰው እንዲተካ ብታደርጉ እጅግ ውብ የሆነ የፍቅርና የስምምነት መንፈስ ይገኛል።

ልክ እንደ እሳት አንደበት «ነገሮችን ለማቀጣጠል» ይችላል። ዳዊት እንዲህ ሲል ጽፏል፡- «በአንደበቴ እንዳልስት መንገዴን እጠብቃለሁ፤ ... ልቤም በውስጤ ሞቀብኝ፤ ከማሰቤም የተነሣ እሳት ነደደ፥ በአንደበቴም ተናገርሁ» (መዝ. [39]፡ 1እና 3)። እንዲህ ዓይነቱ ስሜት ኖሮህ ያውቃል? በእርግጥ አጋጥሞህ ይሆናል። በንዴት አእምሮአችንና ልባችን ሲቃጠል በኋላ የምንጸጸትባቸውን በቁጣ የተሞሉ ንግግሮች እንናገራለን። ዳዊት የቁጡነት ስሜት ነበረው። ሊቆጣጠረው ይችል ዘንድ የእግዚአብሔር እርዳታ ያስፈልገው ነበር። ሰሎሞን እንዲህ ብሎ መጻፉ የሚገርም አይደለም፡- «ጥቂት ቃልን የሚናገር አዋቂ ነው፥ መንፈሱም ቀዝቃዛ የሆነ አስተዋይ ነው» (ምሳሌ 17:27)። «ለትዕግሥተኛው ሰው ብዙ ማስተዋል አለው፤ ቁጡ ግን ስንፍናውን ከፍ ከፍ ያደርጋል» (ምሳሌ 14:29)።

እሳት በትንሹ ጀምሮ በማደግ ሙቀትን መፍጠር ብቻ ሳይሆን ብልሽትም ያስከትላል። አንድ ጓደኛዬ በሚኖርበት ፎቅ ሥር ካለው ምድር ቤት የሚወጣ የእሳት ጭስ ነበር። ከምድር ቤቱ የሚወጣው ጭስና እሳት በፎቁ ላይ ባደረሰው ጉዳት ምክንያት ቤቱ እንደገና እስኪታደስ ድረስ ከነቤተሰቡ ስፍራውን መልቀቅ ግድ ሆኖበት ነበር። እንደ እሳት የሚንበለበል የቁጣ ንግግር ቤትን፥ የእሑድ ትምህርት ቤት ክፍልንና ቤተ ክርስቲያንን ሊያረክስ ይችላል። ይህንን ርኩሰት አጥቦ ሊያስወግድ የሚችል የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

እሳት እንደሚያቃጥልና እንደሚጎዳ አንደበታችንም ሊያቃጥልና ሊጎዳ ይችላል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በተመላለሰበት ጊዜ ከሚያሳዝኑት ነገሮች አንዱ ጠላቶቹ ስለ እርሱ የሚናገሩት ነገር ነበር። «በላተኛና የወይን ጠጅ ጠጪ» ይሉት ነበር (ማቴ. 11:19)። ሰዎች በሚጋብዙት ጊዜ ግብዣቸውን በደስታ ይቀበል ስለነበር ፈሪሳውያን አልወደዱለትም ነበር። ተአምራትን በሚያደርግበት ጊዜ ይህን የሚያደርገው በአጋንንት አለቃ በብዔል ዜቡል ነው አሉት።

በመስቀል ላይ ሆኖ ለሞት በሚያጣጥርበት ጊዜ እንኳ ጠላቶቹ አልተዉትም ነበር። ከክፉ ባሕርያቸው የመነጨ የሚያሳፍር ንግግር ይናገሩ ነበር።

እሳት እየተስፋፋ የሚሄድ ነገር ነው፤ በተለይ በርከት ያለ ነዳጅ ባደረክበት ቁጥር ስፋቱ እየጨመረና በፍጥነት እያደገ ይሄዳል። «አንደበት ... የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል» (ያዕ. 3፡6)። የዚህ ቃል አባባል ሕይወትን በሙሉ በእሳት ላይ ያስቀምጣል እንደማለት ነው። ያዕቆብ ሕይወት በሙሉ እንደ ሰንሰለት የተያያዘ ነውና ነገሮች እንዳይስፋፉ ለማድረግ አንችልም የሚል አሳብ መስጠቱ ነበር። የአንድ ሰው መላ ሕይወት በአንደበት ሊጎዳ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊጠፋ ይችላል። ጊዜ የአንደበትን ኃጢአት ሊያስተካክል አይችልም። በአንደበታችን የፈጸምናቸውን ኃጢአቶች ልንናዘዝ እንችላለን፤ እሳቱ ግን መስፋፋቱን ይቀጥላል።

እሳት እየተስፋፋና እየተዛመደ በሄደ ቁጥር እያጠፋ ይሄዳል፤ የምንናገራቸውም ቃላት የማጥፋት ኃይል አላቸው። በ2ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት «ማይን ካምፍ» ተብሎ በሚጠራው የሂትለር መጽሐፍ ውስጥ በሚገኙ በእያንዳንዱ ቃላት የ125 ሰዎች ሕይወት ጠፍተዋል። በእርግጥ ከእኛ አንደበት የሚወጡ ቃላት ለጦርነቶች ምክንያት ላይሆኑ፥ ወይም ከተሞችን ላያጠፉ ይችላሉ። ነገር ግን የብዙ ሰዎችን ልብ ሊያሳዝኑና ሰብአዊ ክብራቸውን ሊያጠፉ ይችላሉ። ሰዎች ክርስቶስን ሳይቀበሉ እንዲሞቱ በማድረግ ነፍሳትን ሊያጠፉም ይችላሉ። ስለዚህ ንግግራችን በማንኛውም ጊዜ «በጨው እንደተቀመመ፥ በጸጋ» ሊሆን ይገባዋል (ቆላ. 4፡6)።

አንደበት እንደ እሳት ብቻ ሳይሆን እንደ አደገኛ እንስሳም ጭምር ነው። በቁጥጥር ሥር ለማዋል እጅግ የሚያስቸግር ዕረፍት የሌለው ነው። ወጥመድን ዘርግቶ በማጥመድ ይገድላል። እኔና ባለቤቴ ሰፋሪ በሚባል የእንስሶች መጠበቂያ ስፍራ በምንዘዋወርበት ጊዜ ተፈጥሮ ባመቻቸላቸው ሁኔታ ወዲያና ወዲህ የሚዘዋወሩትን የዱር እንስሶች በማየት እንደነቅ ነበር። በስፍራው ዙሪያ ግን እንዲህ የሚል ማስጠንቀቂያ ተለጥፎ ነበር። «ከመኪናችሁ መውረድም ሆነ መስኮቶችን መክፈት አደገኛ ነው።» እነዚያ ሰላማዊ የሚመስሉ የዱር እንስሳት ከፍተኛ ጥፋትን የማስከተል ችሎታ ነበራቸው። ለመግደልም እንኳ ይችሉ ነበር።

አንዳንድ እንስሳት መርዘኛ እንደሆኑ ሁሉ አንዳንድ አንደበቶችም መርዝን ይዘራሉ። መርዝን አደገኛ የሚያደርገው በዝግታ በስውር የሚገድል መሆኑ ነው። አንዳንድ ክፉ ሰዎች ሌሎችን ለመጉዳት ሆን ብለው በንግግራቸው መሐል እንደመርዝ የሆኑ ነገሮችን ይጨምራሉ። መጋቢ እንደ መሆኔ መጠን መርዛማ የሆኑ አንደበቶች በግለሰቦች፥ በቤተሰብ፥ በጎብረተሰብ ክፍሎችና በአጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ጥፋት እንዳደረሱ ተመልክቻለሁ። የተራቡ አናብስትን ወይም የተቆጡ እባቦችን በእሑድ ጠዋት አገልግሎታችሁ የዋሆች ልታደርጉ ትችላላችሁ? በፍጹም! አንደበታቸውን የማይገቱ ሰዎች የሚያስከትሉትም ነገር ከዚህ ጨርሶ የማይለይ ነው።

ያዕቆብ እንስሳትን መግራት ወይም ማስለመድ እንደሚቻል ነግሮናል። በእርግጥ እሳትንም መቆጣጠር ይቻላል። እንስሳትን በምንገራቸው ጊዜ አጥፊ ሳይሆን የሚጠቅሙ አገልጋዮች እናደርጋቸዋለን። እሳትንም በምንቆጣጠርበት ጊዜ ኃይልን እናገኛለን። አንደበትን መግራት የሚችለው ግን ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር እራሱ ነው። አንደበታችን «በገሃነም እሳት መቃጠል» አያስፈልገውም (ያዕ. 3:6)። ለሐዋርያት በበዓለ ኃምሳ ቀን እንደሆነው ከሰማይ በሆነ እሳት ሊለኮስ ይችላል። እግዚአብሔር እሳቱን ከለኮሰውና እራሱ ከተቆጣጠረው የጠፉትን ለክርስቶስ በመማረክና ቤተ ክርስቲያንን በመገንባት አንደበት ትልቅ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። በእርግጥ ዋናውና ማዕከላዊው ነገር ልብ ነው። «በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና» (ማቴ. 12:34)። ልባችን የተሞላው በጥላቻ ከሆነ ሰይጣን እሳቱን ይለኩሳል፤ ልባችን የተሞላው በፍቅር ከሆነ ግን እግዚአብሔር እሳቱን ይለኩሳል።

ደስተኛ የመሆን ኃይል፡- ምንጭና የሚያፈራ ዛፍ፥ (3:9-12)

ምንጭ ሰውን በሕይወት ለማቆየት የሚረዳ ቀዝቃዛ ውኃን ይሰጣል። ምሥራቅ አገሮች ንጹህ ውኃን የሚያመነጭ ምንጭ ማግኘት ለአንድ መንደር ታላቅ በረከት ነው። ሰው ውኃ የሚያስፈልገው ለመጠጥ ብቻ ሳይሆን ለመታጠብ፥ ለማብሰል፥ ለእርሻና ለሌሎችም በርካታ ተግባራት ነው። «የሰው አፍ ቃል የጠለቀ ውኃ ነው፥ የጥበብም ምንጭ ፈሳሽ ወንዝ ነው» (ምሳሌ 18:4)። «የጻድቅ አፍ የሕይወት ምንጭ ናት» (ምሳሌ 10:11)። «የጠቢብ ሰው ትምህርት የሕይወት ምንጭ

ነው» (ምሳሌ 13፡14)። እነዚህ ጥቅሶች ያዕቆብ ስለምንናገራቸው ቃላት አበክሮ የጻፋቸውን ነገሮች በአዎንታዊ ጎኑ የሚደግፉ ናቸው።

ውኃ ሕይወትን ሰጪ እንደሆነ ሁሉ ንግግራችንም ሕይወትን መስጠት ይችላል። ሆኖም ውኃን በሚገባ እየተቆጣጠርን ካልተጠቀምንበት ጥፋትንና ሞትን ሊያስከትል ይችላል። በፔንስልቫንያ የምትገኘው ጆንስታውን ከተማ በ1889 እ.ኤ.አ. በጎርፍ በተመታች ጊዜ የ2200 ሰዎች ሕይወት አልፎአል፤ ወደ 10 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ግምት ያለው ንብረት ደግሞ ጠፍቷል። «ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው» (ምሳሌ 18፡21)።

ቀዝቃዛ ውኃ ለመጠጣት ወደ አንድ ምንጭ በምናነብስበት ጊዜ ስለ ጎርፍ የምናስብበት ምክንያት እንደማይኖር እርግጥ ነው። ከምንጠጣው ውኃ ስለምናገኘው እርካታ ብቻ እናስባለን። ያለ ውኃ ጤነኛ ልንሆን አንችልም «እንደሚዋጋ ሰይፍ የሚለፈልፍ ሰው አለ፤ የጠቢባን ምላስ ግን ጤና ነው» (ምሳሌ 12፡18)። ጳውሎስ ሮምን ለመጎብኘት ባቀደ ጊዜ በሮም የሚገኙትን ቅዱሳን ያነቃቃቸውና ደስ ያሰኛቸው ዘንድ ጸልዮ ነበር (ሮሜ 15፡32)። እርሱን ያነቃቁትን ደስ ያሰኙትን ክርስቲያኖች ስም ይጠቅስ ነበር (1ኛ ቆሮ. 16፡18፤ ፊልሞና 7፡20)።

የውኃ ሌላው ጥቅሙ ማንጻት ነው። በብሉይ ኪዳን የመገናኛ ድንኳን ውስጥ ካህናቱ እጃቸውንና እግራቸውን በመታጠብ የሚነጹበት ውኃ የሚቀመጥበት ዕቃ ነበር። እኛን የሚያነጻን መንፈሳዊ ውኃ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ዮሐ. 15፡3፤ ኤፌ. 5፡26-27)። ለሌሎች የምናካፍለው ቃላችንም የሚሰሙንን ሊያነጻና ሊቀድስም ይችላል። የምንናገረው ቃል የሚነካውን ሁሉ ሕይወትን እንደሚሰጥ በሕዝቅኤል 47 እንደተጠቀሰው ወንዝ መሆን አለበት።

በተጨማሪ፥ አንደበት ደስ የሚያሰኝ ነው፤ ምክንያቱም ልክ እንደ ዛፍ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምናያቸው አገሮች ሁሉ ዛፎች ለምጣኔ ሀብት በጣም አስፈላጊ ነበሩ። አፈር በውኃ ተሸርሽሮ እንዳይወሰድ ይረዱ ነበር፤ ለውበትና ለጥላ ያገለግሉ ነበር፤ ደግሞም ፍሬን ይሰጡ ነበር። የእኛም ቃሎች ለመንገደኛ መጠለያና ማበረታቻ ሊሆኑ ይችላሉ። የተራበ ነፍስን መመገብ ይችላሉ። «የጻድቅ ከንፈሮች ብዙ ሰዎችን ይመግባሉ» (ምሳሌ 10፡21)። ኢየሱስ እንዲህ በማለት ተናግሮ ነበር፦ «... እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው፤ ሕይወትም ነው» (ዮሐ. 6፡3)። የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች በምናካፍልበት ጊዜ

እግረ መንገዳችንን ቃሉን የምናካፍላቸውን ሰዎች እየመገብንና እያበረታታን ነው ማለት ነው።

ለዛፍ ከሁሉም ይልቅ አስፈላጊው ነገር የሥሩ ጉዳይ ነው። ሥሩ በሚገባ በጥልቀት ካልሄደ ዛፉ ጤናማ በሆነ መንገድ ለማደግ አይችልም። በጌታ ነገሮች በሚገባ ሥር የሰደድን ከሆነ የምንናገራቸው ቃሎች ከእርሱ ጋር ያለን የጎበረት ፍሬ ይሆናሉ። በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 1 ላይ እንደምናገኘው በማንኛውም ወቅት እንደሚያፈራው «የተባረከ ሰው» እንሆናለን። ጌታ ኢየሱስ ትክክለኛና ተገቢ የሆኑ ቃሎችን በትክክለኛው ጊዜ ለመናገር የቻለበት አንዱ ምክንያት ከእግዚአብሔር አባቱ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ስለነበረውና በየዕለቱ ከሰማይ እርሱን ይሰማ ስለነበር ነው። ስለ እርሱ የተሰጠውን የሚከተለውን ምስክርነት ተመልከት።

«የደከመውን በቃል እንዴት እንደምደግፍ አውቅ ዘንድ ጌታ እግዚአብሔር የተግሩትን ምላስ ሰጥቶኛል፤ ግለዳ ግለዳ ያነቃኛል፥ እንደ ተግሪዎችም ትሰማ ዘንድ ጆሮዬን ያነቃቃል» (ኢሳ. 50:4) «ግለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ» (ማር. 1:35)።

እኔና አንተ የሚጠቅምና ደስ የሚያሰኝ ንግግርን የሚያፈልቅ አንደበት እንዲኖረን ከፈለግን ከጌታ ጋር በየቀኑ ልንገናኝና ከእርሱ ልንማር ይገባናል። «መንፈሳዊ ሥሮቻችንን» በእርሱ ቃል እጅግ የጠለቁ እንዲሆኑ ማድረግ አለብን። በጸሎትና በጥሞና ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ልቦናችንን በእግዚአብሔር ፍቅርና እውነት እንዲሞላልን መፍቀድ አለብን።

ነገር ግን ያዕቆብ ማስጠንቀቂያን ደግሞ ይሰጠናል፡- አንድ ምንጭ ሁለት ዓይነት ውኃን ሊሰጥ አይችልም፤ ደግሞም አንድ ዛፍ ሁለት ዓይነት ፍሬን ሊሰጥ አይችልም። አንድ ምንጭ ሁልጊዜ ጣፋጭ የሆነ ውኃን እንዲያመነጭ ይጠበቅበታል። ደግሞም የበለስ ዛፍ በለስን ሲያፈራ፥ የወይን ዛፍም ወይንን ያፈራል። ተፈጥሮ የሚያራባው የራሱን ዓይነት ነው።

አንደበት የሚያወጣቸው ቃሎች እርስ በርስ የሚጋጩ ከሆነ በልብ ውስጥ አንድ ከፍተኛ የሆነ ስሕተት አለ ማለት ነው። አንድ ጊዜ በተሰግራበት የሥራ መስክ እጅግ የተናደደና ከአንደበቱ የማይጠበቅ እርግማን ቃል አንድ ከርስቲያን ሲናገር ሰማሁ። ቆይቶ እጅግ አፍሮ ተመለሰና ለሸሪኩ እንዲህ አለው፡- «ያንን ለምን እንዳልኩ አይገባኝም፥ በእውነት በውስጤ የነበረ ነገር አይደለም።» ሸሪኩ በጥበብ እንዲህ ብሎ

መለሰለት፡- «በውስጥህ የነበረ መሆን አለበት፥ ባይሆን ኖሮ ከውስጥህ አይወጣም ነበር።» ጴጥሮስ ከክርስቶስ ጋር ከነበረው ጎብረት ውጪ በሆነ ጊዜ አላውቀውም ብሎ በመሐላ ጌታን ካደ። ወዲያውኑ ግን ወደ ውጭ ወጣና ምርር ብሎ በማልቀስ ኃጢአቱን ተናዘዘ።

እግዚአብሔር አብን የሚባርከና ወዲያውኑ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሰው የሚረግም አንደበት በአስቸኳይ መንፈሳዊ መድኃኒት የሚያስፈልገው ነው። በአምልኮ ፕሮግራም ወቅት መዝሙራትን መዘመርና ከፕሮግራሙ በኋላ ግን እየተከራከሩና እየተጣሉ ወደ ቤት መመለስ እንዴት አሳፋሪ ነው! «ወንድሞቼ ሆይ እነዚህ ነገሮች እንደዚህ መሆን የለባቸውም።»

በእርግጥ ችግሩ ከልብ እንጂ ከአንደበት አይደለም። «መራራ ቅንዓትና አድመኝነት» በልባችን ሊኖር (3፡14) እጅግ ቀላል ነው። «ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይወጣል፥ ሰውንም የሚያረክሰው ያ ነው» (ማቴ. 15፡18)። «አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና» (ምሳሌ 4፡23)። ልባችንን በእግዚአብሔር ቃል በሞላንና ለመንፈስ ቅዱስ በሰጠን ቁጥር ለሌሎች የምንጠቅምና ደስታን የምንፈጥር፥ የሚያነቃቁ ምንጮችና ዛፎች እንሆናለን።

ይህንን ምዕራፍ ለማጠቃለል ሕይወትህን በተሐድሶ ሊለውጡ የሚችሉ ሰባት ቃሎችን መጠቀም እንድትጀምር ላሳስብህ እወዳለሁ። በሚከተሉት ቃሎች መጠቀም ብትጀምር፥ ከአንደበትህ ሲወጡ በእርግጠኝነት ከልብህ እያልካቸው ከሆነ፥ ለሌሎች በረከትና ማጽናኛ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር ይጠቀምባቸዋል። እነዚህ ቃሎች አምስት ብቻ ቢሆኑም ለዚህ ዓላማ የሚሠሩ ናቸው።

«እባክዎትን» እና «አመሰግናለሁ» እነዚህን ሁለት ቃሎች በምትጠቀምበት ጊዜ ሌሎች ሰዎችን እንደ ዕቃ ሳይሆን እንደ ሰው ቆጠርካቸው ማለት ነው። አድናቆትን አሳየሃቸው ማለት ነው።

«አዝናለሁ» (አጥፍቻለሁ ይቅርታ) ይህ ቃል ደግሞ በግንኙነት መሐል ያሉ ግድግዳዎች የሚያፈርስና ድልድዮችን የሚያበጅ ነው።

«እወድሃለሁ» ብዙ ሰዎች በዚህ ቃል ውስጥ የሚመለከቱት «ሥጋዊ ፍቅርን» ነው። ነገር ግን ከዚያ የጠለቀ ትርጉም አለው። እንደ ክርስቲያን ወንድሞቻችንን ጠላቶቻችንንም እንኳ ቢሆን መውደድ አለብን። «እወድሃለሁ» የሚለው ቃል እጅግ ከፍተኛ ኃይል አለው።

«እየጸለይኩልህ ነው» ይህ ቃል ከመናገርህ በፊት እንደምታደርገው እርግጠኛ መሆን አለብህ። ስለ ሰዎች ለእግዚአብሔር መናገር ከቻልህ፣ ስለ እግዚአብሔር ደግሞ ለሰዎች መናገር ትችላለህ። በግላችን ለሰዎች የምናደርገው ጸሎት በሕዝብ ፊት ከሰዎች ጋር ለሚኖረን ግንኙነት የሚጠቅም ነው። እራሳችንን ከሌሎች ይልቅ መንፈሳዊ በሚያደርግ ሁኔታ «እየጸለይኩልህ(ልሽ) ነው» በማለት ትምክሕተኛነታችንን ማሳየት አይገባም። ወደ ጸጋ ዙፋኑ ፊት ይዘናቸው ለመቅረብ የሚያስችለንን ያህል ስለ እነርሱ እንደምናስብ ሌሎች አውቀው ሊበረታቱ በሚችሉበት መንገድ ልንናገረው ይገባል።

አዎን ትንሽ ሆና በዓለም ላይ ታላላቅ ችግሮችን የምትፈጥር አንደበት ናት። ይሁን እንጂ የግድ ችግር ፈጣሪ መሆን የለባትም። እግዚአብሔር ሌሎችን ወደ ሕይወት መንገድ ለመምራት፤ በሕይወት ፈተናዎች ውስጥ ሊያቆማቸውና ደስ ሊያሰኛቸው በሚችል ሁኔታ በአንደበታችን መጠቀም ይቻላል። አንደበት ከአካል ክፍሎቻችን አነስተኛው አካል ቢሆንም ታላቅ ኃይል ግን አለው።

አንደበትህንና ልብህን በየዕለቱ ለእግዚአብሔር ስጥ፤ ለሌሎች በርከት አድርጎ እንዲጠቀምብህ ጸልይ።

ያዕቆብ 3፡13-18

«ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማነው? በመልካም አኗኗሩ ሥራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ። ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኝነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ፥ አትመኩ በእውነትም ላይ አትዋሹ። ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም ነገር ግን የምድር ነው፥ የሥጋም ነው፥ የአጋንንትም ነው፤ ቅንዓትና አድመኝነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሥራ ሁሉ አሉና። ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፥ በኋላም ታራቂ፥ ገር፥ እሺ ባይ- ምህረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፥ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት። የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉት ሰዎች በሰላም ይዘራል።»

ጥበብ የት እንደምትገኝ

ለአይሁድ ሕዝብ ጥበብ በጣም አስፈላጊ ነገር ነበር። እውቀት ብቻ በቂ እንዳልሆነ ተገንዝበው ነበር። እውቀትን በትክክለኛ መንገድ ለመጠቀም ጥበብ አስፈላጊ እንደሆነ ተረድተው ነበር። ሁላችንም ብንሆን በጣም ብልህና ከሁሉ የላቀ ችሎታ ያላቸው ሰዎች እናውቅ ይሆናል። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች የሕይወት ቀላል ተግባራትን እንኳ መፈጸም አቅቶአቸው እናያለን። በኮምፒዩተር ሲጠቀሙና ሲሠሩ እናያለን፤ የራሳቸውን ሕይወት ግን በሚገባ መቆጣጠር አይችሉም። «ጥበብ ዓይነተኛ ነገር ናትና ጥበብን አግኝ» (ምሳሌ 4፡7)።

ያዕቆብ በጉባኤ አስተማሪ መሆን የሚፈልጉትን ሰዎች ማስጠንቀቁን ይቀጥላል (ያዕ. 3፡1)። በሕዝቡ መካከል መቆምና ቃሎችን መናገር ብቻ በቂ አይደለም፤ ልትናገሩ የምትችሉት አንድ ነገር መኖር አለበት። መንፈሳዊ ጥበብ የሚገኘው ከዚህ ውስጥ ነው። እውቀት ነገሮችን በተናጠል የመመልከት ችሎታ ነው፤ ጥበብ ግን የተናጠል እውቀቶቻችንን የማቀናጀትና የእግዚአብሔርን እውነት ከዕለታዊ ሕይወት ጋር የማዛመድ ችሎታ ነው። ሁላችንም ብንሆን በርካታ መልካም ነገሮች ስለሚናገሩ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ሰምተናል። ነገር ግን ማዕከላዊውን የእግዚአብሔርን መልእክት ለማገናዘብ ያለመቻልና እውነትን ከዕለታዊ ሕይወት ጋር ያለማዛመድ ችግር ይታይባቸዋል። ያዕቆብ የሚናገርለት «ከጥበብ የተለየ እውቀት» እንዲህ ዓይነቱ ነው። ያዕቆብ እውነተኛና ሐሰተኛ ጥበቦችን በሦስት ገጽታዎች ያቀርባቸዋል።

ስለሚገኙበት ስፍራ ያቀረበው ንፅፅር (3፡15፣ 17)

እውነተኛ ጥበብ ከላይ የሚመጣ ሲሆን ሐሰተኛ ጥበብ ግን ምድራዊ ነው። በሌላ አባባል ከእግዚአብሔር የሚመጣ «ሰማያዊ ጥበብ» አለ፤ ደግሞም ከእግዚአብሔር ያልሆነ «ሰው ሠራሽ» ጥበብ አለ። ለጊዜው ምንም ያህል ስኬታማ ቢመስልም ከእግዚአብሔር ያልሆነ ጥበብ መጨረሻው ውድቀት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ጥበብ ምንነት እንደሆነ የሚያሳዩ በርካታ ምሳሌዎች ይዞአል። የባቢሎንን ግንብ የመገንባት ፕሮጀክት ብልህነት የተሞላበትሥራይመስላል፤ ፍጻሜው ግን ውድቀትና ግራ መጋባት ነበር

(ዘፍ. 11፡1-9)። ራብ በከነዓን በተከሰተ ጊዜ አብርሃም ወደ ግብፅ መውረዱ ትክክለኛና በብልህነት የተወሰነ ውሳኔ ይመስላል፤ ውጤቱ ግን ያማረ አልነበረም። (ዘፍ. 12፡10-20) ንጉሡ ሳኦል ታናሹ ዳዊት ከጎሊያድ ጋር ለነበረበት ግጥሚያ የራሱን የጦር ልብስ ማልበሱ ብልህነት መስሎት ነበር፤ የእግዚአብሔር ዕቅድ ግን እንደዚያ አልነበረም (1ኛ ሳሙ. 17፡38-58)። ደቀ መዛሙርት ከኢየሱስ ለመማር ተሰብስቦ በነበረው ብዙ ሺ ሕዝብ ትምህርቱ ባለቀ ጊዜ የየራሱን ምግብ እንዲፈልግ መበተኑ ትክክለኛ ነገር መስሎአቸው ነበር፤ ኢየሱስ ግን ጥቂት እንጀራና ዓሣ ወሰደና ያን ሁሉ ሕዝብ መገበ። በሐዋ. 27 የምንመለከታቸው የሮም የአየር ጥናት አዋቂዎች ከወደቡ ለቅቆ ወደ ሮም ለመሄድ መንቀሳቀስ ብልሃት መስሏቸው ነበር፤ ጳውሎስ ግን አልተስማማም ነበር። በኋላ የተነሣው ማዕበል ከአየር ጥናት አዋቂዎች ይልቅ የጳውሎስ ጥበብ ይሻል እንደነበር አረጋግጦአል። ከሞት ተርፈው በሥራቸው ለመጸጸት ዕድል አገኙ።

የሰው ጥበብ መነሻ ምንድን ነው? «ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም፤ ነገር ግን የምድር ነው፤ የሥጋም ነው፤ የአጋንንትም ነው» (ያዕ. 3፡15)። አማኞች ሦስት ጠላቶች አሉአቸው። እነርሱም፦ ዓለም፥ ሥጋና ዲያብሎስ ናቸው (ኤፌ. 2፡1-3)። እነዚህ ጠላቶች የምድር፥ የሥጋም፥ የአጋንንትም፥ በመባል ተገልጠዋል።

«የዚህ ዓለም ጥበብ» አለ (1ኛ ቆሮ. 1፡20-21)። የዓለም እውቀትንና የዓለም ጥበብን ማምታታት የለብንም! በዚህ ዓለም ሰፊ እውቀት መኖሩ የተረጋገጠ ነው። ሁላችንም ብንሆን የዚህ እውቀት ተጠቃሚዎች ነን። ብዙ ጥበብ ግን የለም። ሰው የዚህ ዓለም ምሥጢራትን እየተረዳ ነው፤ ነገር ግን በዚህ እውቀቱ ምን ማድረግ እንዳለበት አያውቅም። የሚያገኘውና የሚሠራው ነገር ሁሉ በእርሱ ላይ በተቃውሞ የሚነሣ ይሆናል። ከአንድ መቶ ዓመት በፊት ሄንሪ ዲቪድ ቶሮ የተባለው ሰው እንዲህ በማለት አስጠንቅቆ ነበር፦ «ላልተሻሻሉ ፍጻሜዎች የተሻሻሉ መንገዶችን እንፈልጋለን»

በአውቶብስ ወይም በባቡር በምጓዝበት ጊዜ በቦስቶን የሚኖር የታወቀ ቻይናዊ ምሁርን ሰው አስታውሳለሁ። በባቡር ጣቢያ ከዚያ የሩቅ ምሥራቅ ሰው ከጓደኛው ጋር ይገናኝና ከምድር በታች ወዳለው የባቡር መስመር መሄጃው ይዞት በጥድፊያ ይሄዳል። እየተቻኮሉ ሲሄዱ ይህ ሰው ለጓደኛው እንዲህ ይለዋል፦ «አሁን ፈጥነን የሚቀጥለውን ባቡር ብንይዝ ሦስት ደቂቃ እናድናለን አለው።» ረጋ ያለው ቻይናዊ ፈላስፋ

መለሰና «በምናድነው ሦስት ደቂቃ ምን የሚረባ ነገር እናደርግበታለን?» አለው።

ዓለም በራሱ ጥበብ እግዚአብሔርን አላወቀምና በራሱ ጥበብ የእግዚአብሔርን ወንጌል ናቀ። «የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ነውና?» (1ኛ ቆሮ. 1፡18)። በዚህ ዓለም ጥበብ ፍቅር የተነደፈ ግንኛውም ሰው የ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክት የመጀመሪያው ሁለት ምዕራፎችን ሊያነብብና ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሰው ጥበብ የሚለውን መገንዘብ አለበት። የሰው ጥበብ ለእግዚአብሔር ሞኝነት ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡20)። የእግዚአብሔር ጥበብ ደግሞ ለሰው ልጅ ሞኝነት ነው (1ኛ ቆሮ. 2፡14)። የሰው ጥበብ የሚመጣው በምርምር ሲሆን የእግዚአብሔር ጥበብ ግን በመገለጥ ይገኛል። የሰው ዓለማዊ ጥበብ ፍጻሜው ከንቱ ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡19)፤ የእግዚአብሔር ጥበብ ግን ለዘላለም ይኖራል።

ዓለም ከእግዚአብሔር ፊቱን ስላዞረ የእግዚአብሔርን ጥበብ አጥቷል። ሰው እውቀቱን እየጨመረ ሲሄድ ችግሮቹ ደግሞ እየጎሉ ይሄዳሉ። «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው» (ምሳሌ 9፡10)። «በዓይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም» (ሮሜ 3፡18)።

ይህ የሐሰት ጥበብ ሌላም ምንጭ አለው። «የምድር» ማለትም «ተፈጥሮአዊ» ነው። ይህ ቃል በግሪክ ሱኪኮስ የሚል ሲሆን «ሕይወት» ወይም «ነፍስ» የሚል ትርጉም ከሚሰጥ «ሱኪ» ከሚል ቃል የመጣ ነው። ሳይኮሎጂ (ሥነ ልቡና) የሚለው ቃል የመጣውም ከዚሁ ቃል ነው። በ1ኛ ቆሮ. 2፡14፤ 15፡44 እና 46 ሱኪኮስ የሚለው ቃል «ፍጥረታዊ» በሚል ቃል ተተርጉሞአል፤ ይህም «መንፈሳዊ» ለሚለው ቃል ተግራሪ ነው። በይሁዳ 19 ደግሞ «ሥጋዊ» በሚል ቃል ተተርጉሞአል። ዋናው አሳብ ሰው ከውድቀት በኋላ ያለው ተፈጥሮ እግዚአብሔር ከሚሰጠው አዲስ ተፈጥሮ ተግራሪ መሆኑን በማሳየት ላይ ነው። ከእግዚአብሔር መንፈስ የተለየ ከሰው የሚመነጭ ጥበብ አለ።

ይህ ምድራዊ ጥበብ «የአጋንንትም» ደግሞ ነው። አጋንንታዊ ነው የሚለው ትርጉም ከሁሉ በተሻለ ሁኔታ ይገልጸዋል። ሰይጣን በተሳካ ሁኔታ ሔዋንን ካታለለበት ከዘፍጥረት 3 ታሪክ ጀምሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሙሉ ሲፈጸም የሚታይ የእግዚአብሔርን ጥበብ የሚዋጋ «የሰይጣን ጥበብ» በሥራ ላይ ነው። ሰይጣን እንደ እግዚአብሔር ትሆኖለሽ በማለት ሔዋንን አሳመናት። ያ የሕይወት ዛፍ ጠቢብ

እንደሚያደርጋት ነገራት። ከዚያን ድርጊት ጀምሮ ሰዎች የሰይጣንን ሐሰት በማመን የራሳቸው አማልክት ለመሆን ሞክረዋል (ሮሜ 1፡18-25)። ሰይጣን አደገኛ፥ ክፉና አታላይ ነው፤ እርሱ የቀድሞው እባብ ነው። የእግዚአብሔርን ጥበብ የማይረዳውን ሰው ሁሉ የሚያምታታና ግራ የሚያጋባ የራሱ ጥበብ አለው።

የምድር፥ የሥጋና የአጋንንት ከሆነው ከዚህ ጥበብ በተፃራሪ ያዕቆብ ስለ «ላይኛይቱ ጥበብ» ይናገራል (ያዕ. 3፡17)። መልካምና ፍጹም የሆነ ስጦታ በሙሉ ከላይ ነው (ያዕ. 1፡17)። ክርስቲያን ለሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ወደ ሰማይ መመልከት አለበት። እግዚአብሔር አባቱ በሰማይ እንዳለ ሁሉ (ማቴ. 6፡9) ዜግነቱ ሰማያዊ ነው (ፊልጵ. 3፡20)፤ መዝገቡም በሰማይ ነው (ማቴ. 6፡19-34)። ኢየሱስ ክርስቶስን ባመነ ጊዜ ከላይ ተወልዶአል (ዮሐ. 3፡1-7)። የአማኝ ቤቱ በሰማይ ነው፤ (ዮሐ. 14፡1-6)፤ ተስፋውም በሰማይ ነው። ፍላጎቶቹንና ትኩረቱንም በምድራዊ ነገር ላይ ሳይሆን በሰማያዊ ነገሮች ላይ ያደርጋል (ቆላ. 3፡1-4)።

የክርስቲያን ጥበብ ምንድን ነው? የዚህን ዓለም ፍልስፍና መፈለግ አለበትን? በፍጹም! መጀመሪያውኑ የእኛ ጥበብ ክርስቶስ ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡24፥ 30)። በክርስቶስ «የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ» አለ (ቆላ. 2፡3)። የእውነተኛው ጥበብ የመጀመሪያ ደረጃ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝ መቀበል ነው።

ደግሞም የእግዚአብሔር ቃል ጥበባችን ነው። «...እንዲህ ታደርጉ ዘንድ አምላኬ እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ ሥርዓትንና ፍርድን አስተማርኋችሁ። ጠብቁአት አድርጉአትም፤ በእውነት ይህ ታላቅ ሕዝብ ጠቢብና አስተዋይ ሕዝብ ነው በሚሉ በአሕዛብ ፊት ጥበባችሁና ማስተዋላችሁ ይህ ነውና» (ዘዳ. 4፡5 ና 6)። ቅዱሳት መጻሕፍት «ኢየሱስን በማመን መዳን» የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡን ይችላሉ (2ኛ ጢሞ. 3፡15)።

ያዕቆብ 1፡5 በእምነት በሚደረግ ጸሎት ጥበብን ማግኘት እንደሚቻል ያመለክታል። «ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግሥና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን።» የእግዚአብሔር መንፈስ «የጥበብና የመገለጥ መንፈስ» ነው (ኤፌ. 1፡17)። በቃሉ በመደገፍ ጸሎታችንን ብናቀርብ ከሁሉም በሚበልጥ በጥበብ መንገድ ይመራናል።

የእውነተኛ መንፈሳዊ ጥበብ ምንጭ እግዚአብሔር ነው። ጥበብን ከማንኛውም ሌላ ምንጭ ማግኘት ችግርን መጋበዝ ነው። ከእግዚአብሔር ተፃራሪ የሆነውን የዓለምን ጥበብ የምንፈልግበት አንዳችም ምክንያት የለም። ይህ የዓለም ጥበብ የሥጋን ፍላጎት የሚያሟላና የዲያብሎስን ተግባር የሚፈጽም ነው። ጥበብን ከእግዚአብሔር ዘንድ አግኝ!

የአሠራር ንፅፅሮች (3፡13-14፥ 17)

ከላይ የሆነው የእግዚአብሔር ጥበብ የሚሠራው ምድራዊ፥ ሥጋዊና ዲያቢሎሳዊ የሆነው ጥበብ ከሚሠራበት መንገድ ፈጽሞ የተለየ ነው። እጅግ ከተለያየ ምንጭ የሚገኙ ስለሆነ የሚሠሩባቸውን መንገዶች ተቃራኒ መሆን አለባቸው።

የሐሰተኛ ጥበብ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

ቅንዓት (3፡14)፡- ይህ ቃል ስለታምነትንና ክፉ ምኞትን የሚገልጥ ነው። በምዕ. 3 የመጀመሪያው ቁጥር ላይ ያዕቆብ ለመንፈሳዊ አገልግሎቶች ክፉት የሞላበት ጽኑ ምኞት እንዳይኖራቸው ካቀረበው ማስጠንቀቂያ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። የዓለም ጥበብ፡- «እራስህን ከፍ አድርግ። ከሌሎች የማታንስ ነህ፤ ምናልባትም ትሻል ይሆናል! ፈጥነህ እንድትሰማ አብልጠህ ጩኽ።» የሚያሳዝነው ነገር ዛሬም ቢሆን በእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል ሥጋዊ የስግብግብነት ስሜትና ተግባር እንዳለ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት እንኳ ሳይቀሩ ከመካከላችን ታላቅ ሰው ማን ነው? በሚል ጉዳይ ተጣልተዋል።

በመንፈሳዊ ቅናት ስም የራስን የስስት ፍላጎት ማራመድ ይቻላል። ፈሪሳውያን ሃይማኖታዊ ተግባሮቻቸውን ከሰዎች ምስጋና ለማግኘት ይጠቀሙባቸው ነበር (ማቴ. 6፡1-18)። በጌታ ጉዳዮች ቀናተኛ መሆን አለብን፤ የቅናታችን እውነተኛ ምክንያት ቀና መሆኑን ግን ማረጋገጥ አለብን። የዚህ ዓለም ጥበብ ሰውን ከፍ ከፍ በማድረግ የእግዚአብሔርን ክብር ይጋፋል። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 1፡17-31 ላይ የእግዚአብሔርና የዚህ ዓለምን ጥበብ በመተንተን እግዚአብሔር ተግባራቱን በዚህ መንገድ የሚፈጽምበትን ምክንያት ይገልጣል። «ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ» (ቁ. 29)። ይህንንም ክፍል በሚቀጥለው ምክር ያጠቃልላል፡- «የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ» (ቁጥር 31)።

ለጌታ ያለን ቅንዓት መንፈሳዊ ነው ወይስ ሥጋዊ? ሌሎች በማይሳካላቸው ጊዜ በኃዘን ሸክማቸውን እንካፈላለን ወይስ ደስ

እንሰኛለን? የዓለም ጥበብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ሥጋዊ የሆነ አድናቆትና ሰብአዊ ክብር እየገነነ ይሄዳል። ተጠንቀቁ!

አድመኝነት (3፡14)፡- የዚህ ቃል ትርጉም «የቡድን መንፈስ» ማለት ነው። በግሪክ የዚህ ቃል ትርጉም ድምፅን ለመሰብሰብ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ቅስቀሳ የሚያደርግ ፖለቲከኛን የሚያመለክት ነው። የዓለም ጥበብ እንዲህ ይላል፡- «የምትችለውን ያህል ድጋፍ ሰብስብ፤ በቤተ ክርስቲያንህ ያሉ ሰዎች የአንተ ደጋፊዎች ወይም ተቃዋሚዎች መሆናቸውን አረጋግጥ።» በእርግጥ የራስን ብቻ የመፈለግ የስስታምነት ስሜት ውጤት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልና መሪርነትን ይፈጥራል። «ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ ስንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር» (ፊልጵ. 2፡3)።

መመካት (3፡14)፡- ትዕቢት ትምክሕተኛ ነው። ከሰው ጥበብ የላቀ ደግሞ ትምክሕተኛ የለም። ለእግዚአብሔር ክብር እንደሆነ ስለ በረከቶቹ የምንመሰክርበት መንገድ አለ፤ ነገር ግን ምስጋናና ክብርን ለሰው የሚሰጥ አቀራረብ አለ። በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል እርስ በርስ የመወዳደስ ስሜትን ማየት አሳፋሪ ነው። በ2ኛ ቆሮ. 10 ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ በትምክሕት ለመናገር በሚገደድበት ጊዜ ክብሩን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጓል። «ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ከአንዳንዶች ጋር ራሳችንን ልንቆጥር ወይም ራሳችንን ልናስተያይ አንደፍርምና፤ ነገር ግን እነርሱ ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር ሲያመዛዝኑ፥ ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር ሲያስተያዩ፥ አያስተውሉም» (2ኛ ቆሮ. 10፡12)።

የእግዚአብሔር ጥበብ በውስጥህ በሚሠራበት ጊዜ የትሕትናና ራስን የማስገዛት ስሜት በውስጥህ ያድራል። ክብሩንም ሁሉ ለእግዚአብሔር ትሰጣለህ። እራስህን ከማንኛውም ክርስቲያን ጋር የማወዳደር ፍላጎት አይኖርህም። ክርስቶስን ብቻ በማየት እራስህን ከእርሱ ጋር ብቻ ታወዳድራለህ። ምክንያቱም ራሳችንን ከክርስቶስ ጋር ስናወዳድር ገና ብዙ የሚቀረን ነገር እንዳለ እንገነዘባለን።

በእውነት ላይ መዋሸት ወይም ማታለል (3፡14)፡- «በእውነትም ላይ አትዋሹ» ቅደም ተከትሉን መረዳት አስቸጋሪ አይደለም። በመጀመሪያ ወደ ቡድን መንፈስና ወደ ፉክክር የሚመራ የስስታምነት ጽኑ ፍላጎትና አሳብ ይመጣል። በምርጫው አሸናፊነት ለማግኘት ደግሞ በትምክሕት መናገር ይከተላል። ብዙ ጊዜ የትምክሕት ንግግር ደግሞ

ውሸት ይኖረዋል። የሰው ሕይወት በውጫዊ መግለጫ አይታወቅም፤ በልቡ ያለውን ግን ጌታ ብቻ ነው የሚያውቀው። «ስለዚህም በጨለማ የተሰወረውን ደግሞ ወደ ብርሃን የሚያወጣ የልብንም ምክር የሚገልጥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ጊዜው ሳይደርስ አንዳች አትፍረዱ፤ በዚያን ጊዜም ለእያንዳንዱ ምስጋናው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሆናል» (1ኛ ቆሮ. 4፡5)።

ወደ እውነተኛ መንፈሳዊ ጥበብ መመለስ ምንኛ ዕረፍት ነው!

የዋህነት (3፡13)፡- የዋህነት ደካማነት አይደለም፤ በቁጥጥር ሥር የዋለ ኃይል ነው። የዋህ ሰው በስግብግብነት ለራሱ ብቻ አያስብም። ይህንን ቃል የሚገልጸው የግሪክ ቃል ስለ ተገራ በቁጥጥር ሥር የዋለን ፈረስ ጉልበትን ያመለክታል። የዋህ ሰው የእግዚአብሔርን ክብር ብቻ ይፈልጋል እንጂ ከሰዎች ክብርን አይፈልግም። የዋህነት ሰው ሊፈጥረው የማይቻለው የመንፈስ ፍሬ ነው (ገላ. 5፡23)። አንዳንድ ሰዎች የዋህነት አድርገው የሚያቀርቡት እውነተኛ ያልሆነ አስመሳይ የዋህነት አለ። ይህ ግን ግስመሰያ እንጂ የዋህነት አይደለም!

«በጥበብ የዋህነት» የሚለው ቃል በጣም ጠቃሚ ቃል ነው (ያዕቆብ 3፡13)። የዋህነት ኃይልን በትክክለኛ መንገድ መጠቀም ማለት ሲሆን ጥበብ ደግሞ እውቀትን በትክክለኛ መንገድ መጠቀም ማለት ነው። በአንድነት የሚሄዱ ነገሮች ናቸው። እውነተኛ ብልህ ሰው በዕለታዊ ሕይወቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያሳያል። ዝንባሌና ተግባር አይነጣጠሉም።

ንጽሕት (3፡17)፡- «በመጀመሪያ ንጽሕት» የሚለው ቃል የቅድስናን አስፈላጊነት የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። ስለዚህ ከላይ የሆነችው ጥበብ ንጽሕት ናት። ከዚህ ቃል ጀርባ ያለው አሳብ «የሥነ ምግባር ንጽሕናን ከርኩሰት ነፃ መሆንን» የሚያመለክት ነው። ያዕቆብ በምዕራፍ 4 ቁ. 8 «ልባችሁን አጥሩ» ወይም ልባችሁን በሥነ ምግባር የነጻ አድርጉ በማለት እንደገና ተጠቅሞበታል። የእግዚአብሔር ጥበብ ወደ ንጽሕና ሕይወት ይመራል። የሰው ጥበብ ግን ወደ ኃጢአት ይመራል። ከጌታ ጋር ንጹሕ የሆነ ግንኙነትን የሚያመጣ መንፈሳዊ ንጽሕና አለ (2ኛ ቆሮ. 11፡3)። መንፈሳዊ ሰውን አመንዝራ የሚያደርገው ዓለማዊነት ደግሞ አለ (ያዕ. 4፡4)።

ሰላም (3፡17)፡- የሰው ጥበብ ወደ ውድድር፥ ፉክክርና ጦርነት ይመራል (ያዕ. 4፡1-2)። የእግዚአብሔር ጥበብ ግን ወደ ሰላም ይመራል። ይህ በቅድስና ላይ እንጂ እውነትን ለድርድር በማቅረብ ላይ

የተመሠረተ አይደለም። እግዚአብሔር ሰላምን ለመፍጠር ሲል እንደ ቀልድ የሚተወው አንዳችም ነገር የለም። የቤተ ክርስቲያን ሰላም ከቤተ ክርስቲያን ንጽሕና ይልቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር የተሰጠችና ንጽሕት ከሆነች በዚያን ጊዜ ሰላም ይሆናል። «የጽድቅም ሥራ ሰላም የጽድቅም ፍሬ ለዘላለም ጸጥታና መታመን ይሆናል» (ኢሳ. 32፡17)። ቤተ ክርስቲያን ኃጢአት እያለ እንደሌለ አድርጋ በመቁጠርና ችል ብላ በመተው ሰላም ሊኖራት አይችልም። የሰው ጥበብ «ኃጢአትን አትግለጡ፤ የነገሮችን አንድነት ጠብቁ» ይላል። የእግዚአብሔር ጥበብ ግን «ኃጢአታችሁን ተናዘዙ፤ የእኔ ሰላም የነገሮችን አንድነት ይጠብቃል» ይላል።

ገርነት (3፡17)፡- ማቴዎስ አርኖልድ የተባለ ሰው ይህንን «አጥጋቢ ምክንያታዊነት» ብሎ ይጠራዋል። ገርነት ማለት ያለምንም ማቃለል እውነተኛ መሆንን፥ ያለምንም ደካማነት ገር መሆንን ያመለክታል። ገር ሰው ሆን ብሎ ጠብን የሚፈልግ ባይሆንም እንኳ ሰላምን ለማድረግ ብሎ እውነትን ለድርድር የሚያቀርብ አይደለም።

እሺ ባይነት (3፡17)፡- የእግዚአብሔር ጥበብ አንድን አማኝ ከሰው ሁሉ ጋር በስምምነት የሚኖር ሊያደርገው ይችላል። ከእርሱ ጋር መኖር ያስደስታል። የሰው ጥበብ ግን ሰውን ግትርና ዐመፀኛ ያደርገዋል። እሺ ባይ የሆነ ሰው ከሁሉም አቅጣጫ የሚመጡትን ጥያቄዎች ለመስማት ፈቃደኛ ቢሆንም የእራሱን ትክክለኛ አቋም ግን ለድርድር ለማቅረብ ፈቃደኛ አይደለም። በአንዳንድ ነጥቦች ከሰዎች ላይስማማ ቢችልም፥ ይህን የሚያደርገው ያለ ምንም ጠብና ንትርክ ነው። ለመስማት የፈጠነ ለመናገርና ለቁጣ ግን የዘገየ ነው (ያዕቆብ 1፡19)። ብዙ ሰዎች ግትርነት በአቋም መጽናት አድርገው ይቆጥሩታል። እናም የግድ የራሳቸውን መንገድ የሙጥኝ ብለው ይይዛሉ። የእግዚአብሔር ጥበብ በሥራ ላይ በሚሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር የሚገልጠውን ነገር ሁሉ ለመስማት፤ ለማሰብ፥ ለመጸለይና ለመታዘዝ ፈቃደኝነት ይመጣል። የዚህ ቃል ሌላው ትርጉም «አሳማኝ የሆነ ነገርን ለመቀበል እራስን መስጠት» ማለት ይሆናል።

ምሕረት የሞላበት (3፡17)፡- በአንድ ነገር «መሞላት» ማለት በዚያ ነገር «ቁጥጥር ሥር መሆን» ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ጥበብ የሚከተል ሰው በምሕረት ቁጥጥር ሥር ይሆናል። «አባታችሁ ርኅሩኅ እንደሆነ ርኅሩሆች ሁኑ» (ሉቃ. 6፡36)። እግዚአብሔር በጸጋው የማይገባንን ነገር ሰጠን። በምሕረቱ ደግሞ ሊደርስብን የሚገባ ነገር

እንዳይደርስብን አደረገ፤ ጌታ የተናገረው የመልካሙ ሳምራዊ ምሳሌ የምሕረትን ትርጉም የሚያስረዳ ነው (ሉቃ. 10፡25-37)። ሳምራዊ ለአይሁዳዊ ይህን እንክብካቤ ማድረጉ የምሕረት ተግባር ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረጉ ከሚያገኘው በረከት በስተቀር ከዚህ ተግባሩ የሚያገኘው አንዳችም ጥቅም አልነበረም። የተደረገለትም ሰው ብድሩን ለመክፈል አይችልም ነበር። ምሕረት ማለት ይህ ነው።

በጎ ፍሬ የሞላበት (3፡17)፡- ታማኝ የሆኑ ሰዎች ፍሬ ማፍራት ይችላሉ። የእግዚአብሔር ጥበብ ሕይወትን ባዶ ሳይሆን ሙሉ ያደርጋል። መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን ፍሬን ያፈራል (ዮሐ. 15፡1-16 ተመልከቱ)። በሉቃ. 10፡25-37 የምናገኘው ሕግ አዋቂ ስለ ባልንጀራነት ለማውሳት ፈቃደኛቢሆንም፥ ባልንጀራውብመሆን ሌላውን ሰው ለመርዳት ፈቃደኛ አልነበረም። የእግዚአብሔር ጥበብ ተግባራዊ ነው። ሕይወትን በመለወጥ ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን መልካም ፍሬን ያፈራል።

ጥርጥር የሌለባት (3፡17)፡- ቃሉ በአንድ አሳብ መቁረጥን ሲያመለክት የተጠራጣሪነት ተቃራኒ ነው (ያዕ. 1፡6)። በዓለም ጥበብ ላይ በምትደገፍበት ጊዜ በተለያየ ውጫዊ ተጽዕኖ ምክንያት አሳብህን ትለውጣለህ። አዲሱ አመለካከትህ ተጽዕኖ ሊያደርግብህ ይችላል። የእግዚአብሔር ጥበብ በሚኖርህ ጊዜ ማወላወል ወይም ተጠራጣሪነት አይኖርም፤ ወሳኝ ስለምትሆን አትፈራም። ከላይ የሚገኝ ጥበብ ከላይ የሆነ ኃይልን ያመጣል።

ግብዝነት የሌለባት (3፡17)፡- በአዲስ ኪዳን ግብዝነት ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል ትርጉም «ጭምብል የለበሰ ያልሆነውን የሚመስል ቲያትረኛ» ማለት ነው። በሰው ጥበብ ስንመራ ግብዝነትና ማስመሰል ይኖራሉ። የእግዚአብሔር ጥበብ በተግባር ላይ በሚሆንበት ጊዜ ግን ግልጽነት፤ ታማኝነትና እውነትን በፍቅር መነጋገር ይኖራሉ (ኤፌ. 4፡15)። የእግዚአብሔር ሕዝብ በማስመሰልና እርስ በእርስ በመደባበቅ በሚኖርበት ጊዜ አገልግሎቱን የሚቆጣጠረው የሰው ጥበብ እንደሆነ እርግጠኛ መሆን ይቻላል «የሃይማኖታዊ ፖለቲካ» እግዚአብሔር እጅግ የሚጠላው ነገር ነው። የእምነት ኑሮ ግን ያለምንም መደባበቅና ምሥጢረኝነት የምንኖረው ኑሮ ነው።

በዚህ ዓለም ጥበብ አሠራርና በእግዚአብሔር ጥበብ አሠራር መካከል ሰፊና ተነባባሪ ልዩነት አለ። የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናትና መሪዎች ሕይወታቸውንና አገልግሎታቸውን ያዕቆብ በመልእክቱ

በሚለው መመዘን እጅግ አስፈላጊያቸው ነው። ተጠቃሚም ያደርጋቸዋል። አንዲት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድርጅት ብትሆንም እንኳ ዓለማዊ የሆኑ ድርጅቶች ውጤታማ በሚሆኑበት ዘዴ መጠቀም አትችልም። የእግዚአብሔር አሳብና መንገድ ከእኛ እጅግ የላቁ ናቸው። «እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም» (1ኛ ቆሮ. 2፡12)።

የውጤቶች ንፅፅር (3፡16፥ 18)

ውጤትን የሚወስነው መነሻ ነው። ዓለማዊ ጥበብ ዓለማዊ ውጤቶችን ሲያስገኝ መንፈሳዊ ጥበብ ደግሞ መንፈሳዊ ውጤቶችን ያስገኛል።

የዓለማዊ ጥበብ ውጤት ችግር ነው (3፡16)፡- ቅንዓት፥ አድመኝነት፥ ሁከትና ክፉ ሥራ። ጉባኤ ውስጥ እግዚአብሔር እየሠራ አይደለም። ያዕቆብ በምዕራፍ 4 ላይ በአማኞች መካከል ስላለ «ጦርነትና ጠብ» ይናገራል። የተሳሳተ አስተሳሰብ የተሳሳተ አኗኗርን ያስከትላል። ዓለም በዚህ ዓይነት የተዛባ ሁኔታ ውስጥ የሆነችበት አንዱ ምክንያት የእግዚአብሔርን ጥበብ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኗ ነው።

ሁከት ተብሎ የተተረጎመው ቃል የተረጋጋ ሁኔታ ካለመኖሩ የተነሣ የሚመጣን የሥርዓት መዛባት የሚያመለክት ነው። በያዕ. 1፡8 ከምናገኘው «መወላወል» ከሚለውና በያዕ. 3፡8 ከምናገኘው «ወላዋይ ክፋት» ከሚለው ቃል ጋር የተያያዘ ነው። 2ኛ ቆሮ. 12፡20 ብታነብብ ሁከት ያለባት ቤተ ክርስቲያን ምን እንደምትመስል ትመለከታለህ። ኢየሱስ በመጨረሻው ቀን በዓለም ላይ የሚሆነውን አስደንጋጭ ነገር ለመግለጽ ይህንን ቃል ተጠቅሞአል (ሉቃስ 21፡9)።

ቅናት፤ ፉክክርና የቡድን ስሜት ለዚህ ሁከት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። በዘፍ. 11 ላይ የምናገኘው የባቢሎን ግንብ ታሪክ የዚህ እውነታ ጥሩ ማስረጃ ነው። በሰው አመለካከት የባቢሎን ግንብ የመገንባት ሥራ ብልህነት ነበር። ከእግዚአብሔር አመለካከት አንፃር ግን ይህ ሥራ የማይረባና የኃጢአት ሥራ ነው። ውጤቱ ሁከት ነበር። ዛሬም ቢሆን እንኳ ባቢሎን የሚለው ቃል ትርጉም ከግራ መጋባት ጋር የሚሄድ ነው።

ግራ መጋባት «ለክፉ ሥራ ሁሉ» መንገድን የሚያዘጋጅ ነው (ያዕ. 3፡16)። በዚህ ስፍራ ያለው ክፉ የሚለው ቃል «ዋጋ የሌለውና

የማይጠቅም» የሚሉትን ቃሎች የሚወክል ነው። በ1ኛ ቆሮ. 3፡12 ላይ የሚገኙትን «እንጨት፥ ሣርና አገዳ» ያስታውሰናል። በዓለም ጥበብ የሚሰጡ አገልግሎቶች ታላቅና ስኬታማ ሊመስሉ ይችላሉ፤ በፍርድ ቀን ግን ይቃጠላሉ። ስለዚህ «ጊዜው ሳይደርስ አንዳች አትፍረዱ» (1ኛ ቆሮ. 4፡5)። በሰምርኔስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን እንደ ደሀ ተቆጥራ ነበር። ጌታ ግን ሀብታም ነች አለ። በሎዶቅያ የነበረችው ሀብታም ቤተ ክርስቲያን ግን ድህነቷ በገሀድ ተነገረባት (ራእይ 2፡9 ና 3፡14-22)።

በአጥቢያ ቤተክርስቲያናችን ልናደርግ የምንችለው ከሁሉም የላቀ ነገር አገልግሎታችንን በሰዎች ጥበብ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል መመዘን ነው። በክርስቲያኖች መካከል የሚኖሩ በርካታ ጠቦች፥ የቤተ ክርስቲያን መከፋፈል፥ የንጽሕናና የሰላም መታጣት ሁሉም አንድ ችግር እንዳለ ያመለክታሉ። ምናልባት ያ ችግር የእግዚአብሔር ጥበብ መጉደል ውጤት ሊሆን ይችላል።

የእግዚአብሔር ጥበብ በረከትን ያመጣል (3፡18)፡- ያዕቆብ ፍሬ ወደሚል ቃል እንደገና ይመለሳል። በሰው ሠራሽ ውጤቶቹና እግዚአብሔር በሚሰጠው ፍሬ መካከል እጅግ ሰፊ ልዩነት አለ። ፍሬ የሕይወት ውጤት ነው፤ ደግሞም ፍሬ የበለጠ ለማፍራት የሚያስችሉ ዘሮች በውስጡ ይገኙበታል። ብዙ ጊዜ የሚዘራ ዘር ነው፤ በዚህ ስፍራ ግን ፍሬ እራሱ ሲዘራ እንመለከታለን። የእግዚአብሔርን ፍሬ ከሌሎች ጋር በተካፈልን ቁጥር ሰዎች ይመገባሉ፤ ደግሞም ይረካሉ፤ በውጤቱም እነርሱም ፍሬን ያፈራሉ።

የክርስቲያን ሕይወት የመዝራትና የማጨድ ሕይወት ነው። በእርግጥ ማንኛውም ሕይወት የመዝራትና የማጨድ ሕይወት ነው፤ ሁልጊዜ የዘራነውን እናጭዳለን። ለእግዚአብሔር ጥበብ የሚታዘዝ ክርስቲያን የሚዘራው ጽድቅን እንጂ ኃጢአትን አይደለም የሚያጭደው። ሰላምን እንጂ ጦርነትን አይደለም። የምንኖረው ሕይወት ጌታ ጽድቅንና ሰላምን በሌሎች ሕይወት እንዲያመጣ ይረዳዋል።

ማንነታችን ኑሮአችንን ያሳያል። የምናጭደው ደግሞ የዘራነውን ነው። የምንዘራው ነገር የምናጭደውን ነገር ይወስናል። በእግዚአብሔር ጥበብ ከኖርን ጽድቅንና ሰላምን እንዘራለን፤ ደግሞም የእግዚአብሔርን በረከት እናጭዳለን። በሰው ዓለማዊ ጥበብ ከኖርን ኃጢአትንና ጠብን እንዘራለን፤ ሁከትንና ክፉ ሥራዎችን ሁሉ እናጭዳለን።

በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ችግር ፈጣሪ መሆን እጅግ ከባድ ነገር ነው። እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ኃጢአቶች አንዱ

በወንድማማቾች መካከል ጠብን መዝራት ነው (ምሳሌ 6፡16-19 አንብብ)። ሎጥ የዓለምን ጥበብ በመከተሉ ወደ አብርሃም ካምፕ (ድንኳን) ችግርን አመጣ፤ አብርሃም ግን የእግዚአብሔርን ጥበብ በመከተሉ ሰላምን አመጣ። የሎጥ ውሳኔ ለምንም ነገር ወደማይጠቅሙ ሥራዎች የሚመራ ሆነ። ሎጥ የኖረበት ነገር ሁሉ በሰዶምና ገሞራ ጥፋት ምክንያት በነነ። አብርሃም በእግዚአብሔር ጥበብ የወሰነው ውሳኔ በረከትን ለራሱና ለቤተሰቡ በመጨረሻም ለዓለም ሁሉ ወደሚያመጣ ነገር መራው (ዘፍ. 13ን አንብብ)።

«ጥበብን የሚያገኝ ሰው ምስጉን ነው፥ ማስተዋልንም ገንዘቡ የሚያደርግ» (ምሳሌ 3፡13)።

ያዕቆብ 4፡1-12

«በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደሉምን? ትመኛላችሁ ለእናንተም አይሆንም፤ ትገድላላችሁ በብርቱም ትፈልጋላችሁ፥ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ ትዋጉማላችሁ ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤ ትለምናላችሁ፥ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በከፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም። አመንዝሮች ሆይ፥ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል። ወይስ መጽሐፍ በእኛ ዘንድ ያሳደረው መንፈስ በቅንዓት ይመኛል ያለው በከንቱ እንደ ተናገረ ይመስላችኋልን? ነገር ግን ጸጋን አብልጦ ይሰጣል፤ ስለዚህ፡- እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ይላል። እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ፥ ልባችሁን አጥሩ። ተጨነቁና እዘኑ አልቅሱም፤ ሳቃችሁ ወደ ኃዘን ደስታችሁም ወደ ትካዜ ይለወጥ። በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል።

«ወንድሞች ሆይ፥ እርስ በርሳችሁ አትተማሙ። ወንድሙን የሚያማ በወንድሙም የሚፈርድ ሕግን ያማል በሕግም ይፈርዳል፤ በሕግም ብትፈርድ ፈራጅ ነህ እንጂ ሕግን አድራጊ አይደለህም። ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ ነው፤ እርሱም ሊያድን ሊያጠፋም የሚችል ነው፤ በሌላው ግን የምትፈርድ አንተ ማን ነህ?»

ጦርነቶች እንዴት ያከትማሉ?

ስለ ማይጨው ጦርነት ሰምተህ ታውቃለህን? ወይም ስለ ዐድዋ ጦርነት ወይም ስለ ኮሪያ ዘመቻ ሰምተህ ታውቃለህን? እነዚህ በተለያዩ ሕዝቦች መካከል የተደረጉ ጦርነቶች ናቸው። በአብዛኛው የታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ስለ እነዚህ ጦርነቶች እናነብባለን።

በሕዝቦች መካከል የሚደረጉ የተለያዩ ስምምነቶች ቢኖሩም፥ ስለ አቶሚክ ቦንብ የተደረጉ የተለያዩ ስምምነቶች ቢኖሩም፥ ጦርነት ግን የሕይወት እውነታ ነው። በሕዝቦች መካከል ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ሕይወት ገጽታና የተለያዩ ደረጃዎች ጦርነት አለ። ብዙ ሱቆች ባሉባቸው መንደሮች ውስጥ እንኳ እነዚህ ፉክክሮች አሉ።

ያዕቆብ ጦርነትን ዋና ዓላማ አድርጎ በዚህ ክፍል ይናገራል። በዚህ ዓለም ላይ የሚካሄዱ ሦስት የተለያዩ ዓይነት ጦርነቶች እንዳሉ ይገልጻል። እንዴት እነዚህ ጦርነቶች መቆም እንደሚችሉም ይገልጻል።

በሰዎች መካከል የሚደረግ ጦርነት (4፡1፥ 11-12)

«በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ?» በወንድሞች መካከል! «ወንድሞች በጎበረት ቢቀመጡ፥ እነሆ መልካም ነው። እነሆም ያማረ ነው» (መዝ. 133፡1)። በእርግጥ ወንድሞች በፍቅርና በስምምነት መኖር አለባቸው። ብዙ ጊዜ ግን ይህ አይታይም። ሎጥ ከአጎቱ ከአብርሃም ጋር ተጣላ (ዘፍ. 13)። አቤሴሎም ከአባቱ ከዳዊት ጋር ተጣላ (2ኛ ሳሙ. 13፡18)። ደቀ መዛሙርት እንኳ በመካከላችን ታላቅ የሚሆን ማን ነው? እያሉ በመከራከራቸው ምክንያት ለጌታ ችግር ፈጥረውበት ነበር (ሉቃስ 9፡46-48)።

ከጥንት አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ የአንዳንዶቹን ስንመረምር በመካከላቸው ስምምነት እንዳልነበረ እንገነዘባለን። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት በጉባኤ እርስ በእርስ ይፎካከሩ ነበር። ጉዳዮቻቸውን ወደ ፍርድ ቤት እስኪያቀርቡ ድረስ በመካከላቸው ውዝግብ ነበር (1ኛ ቆሮ. 6፡1-8 ና 14፡23-40)። የገላትያ ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው እየተበላሉና እየተነካከሱ ነበር (ገላ. 5፡15)። ጳውሎስ የኤፌሶን ክርስቲያኖች መንፈሳዊ አንድነታቸውን ያሳድጉ ዘንድ ለምኗቸው ነበር

(ኤፌ. 4፡ 1-16)። በቤተ ክርስቲያኒቱ የነበሩ ሁለት ሴቶች ተስማምተው ለመኖር ስላልቻሉና ለጳውሎስ እጅግ ተወዳጅ በነበረችው በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ችግር ተፈጥሮ ነበር (ፊልጵ. 4፡ 1-3)።

ያዕቆብ በቅዱሳን መካከል ስለነበሩት በርካታ የተለያዩ አለመግባባቶች አመልክቶ ነበር።

በመደብ ልዩነት ምክንያት የመጡ ጦርነቶች (2፡ 1-9)፡- በሀብታምና በደሀ መካከል የነበረ ለዘመናት የማያቋርጠው ልዩነትና ውድድር በዚህም እንደ ነበር እንመለከታለን። ሁልጊዜ ሀብታም ሰው ትኩረት ሲያገኝ፥ ድሀው ግን የሚመለከተው አልነበረም። ደግሞ ይናቅ ነበር። ሀብታም ይከበር ደሀው ደግሞ ይናቅ ነበር። የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለሀብታም ሰው እንክብካቤ በማድረግ ድሀውን ንቆ በመተው ወይም በመርሳት የተገላቢጦሽ የሆነ ድርጊት ሲፈጽሙ ማየት እንዴት የሚያሳዝን ነገር ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረግ ጎብረት እንደ ልብስና በመሳሰሉት የኢኮኖሚን ዓቅም በሚገልጹ ነገሮች ላይ የሚመሠረት ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ናት ማለት ነው።

በአሠሪና ሠራተኛ መካከል ያሉ አለመግባባቶች (5፡ 1-6)፡- ድሀውን ሊቆጣጠረውና ሊጎዳው የሚችል ኃይል ያለው ሀብታም ሰው ነው። «ሠራተኞች ከአሠሪያቸው የሠሩበትን ዋጋ ወይም ተገቢ የሆነ ክፍያ አያገኙም ይሆናል። በዘመናችን እንደሚታየው ዓይነት የሠራተኛውን መብት የሚያስጠብቁ ናቸው የሚባሉ ማኅበራት ቢኖሩም እንኳ ጥሩ የማያገኙ ወይም ገቢያቸው ከሚሠሩት ሥራ ጋር ሲመዛዘን ፈጽሞ በቂ ያልሆነ በርካታ ሰዎች አሉ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ግጭቶች (1፡ 19-20፤ 3፡ 13-18)፡- ያዕቆብ ይህንን መልእክት የሚጽፍላቸው አማኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የኃላፊነትና የሥልጣን ስፍራ ግጭት ወይም ጦርነት ከፍተው እንደ ነበር ደግሞ ግልጽ ነው። ብዙዎቹ አስተማሪዎች ወይም መሪዎች መሆን ፈልገው ነበር። ቃሉን በሚያጠኑበት ጊዜ ውጤቱ መንጻትና መገንባት ሳይሆን ዐመፅና ክርክር ሆኖ ነበር። እያንዳንዱ ሰው የራሱ አሳብ ብቻ ትክክል እንደሆነ፥ የራሱ መንገድ ብቻ እውነተኛውና ትክክለኛው መንገድ እንደሆነ ያምን ነበር። ጉባኤዎቻቸውን መንፈሳዊ መሰጠት ሳይሆን ስግብግብነት ገዝቶአቸው ነበር።

በወንድማማቾች መካከል የነበሩ ጦርነቶች (4፡ 11-12)፡- ቅዱሳን አንዱ በአንዱ ላይ ክፉን ይናገር፥ ይተማማና ይፈርድ ነበር።

በዚህም ስፍራ እንደገና አንደበትን ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ የመጠቀምን ሁኔታ እናያለን። ክርስቲያኖች እውነትን በፍቅር ሊነጋገሩ ይገባል (ኤፌ. 4፡15)። በውድድር፥ በመቀናናትና በትችት መንፈስ ክፉ ነገሮችን ሊነጋገሩ አይገባም። ስለ አንድ ወንድም የምናውቀው እውነት ጎጂ ነገር ከሆነ በፍቅር ልንሸፍነው እንጂ ደጋግመን ልናነሣው አይገባም (1ኛ ጴጥ. 4፡8)። ኃጢአትን ካደረገ በግሉ ልናነጋግረውና ጉዳዩን ከጌታ ጋር እንዲያስተካክል ልንረዳው ይገባል (ማቴ. 18፡15-19፤ ገላ. 6፡1-2)።

ያዕቆብ መለየትን ወይም ደግሞ ሰዎችን መገምገምን አይደለም የሚከለክለን። ክርስቲያኖች የሚሻለውን ነገር ፈትነው መውደድ አለባቸው (ፊልጵ. 1፡9-10)። ነገር ግን በእግዚአብሔር ስፍራ ሆነው በሌሎች ላይ መፍረድ የለባቸውም። በመጀመሪያ እራሳችንን ልንመረምርና ቀጥሎም ሌሎችን ለመርዳት ልንጥር ያስፈልጋል (ማቴ. 7፡1-5)። በአንድ ጉዳይ ውስጥ የሚኖሩትን እውነታዎች ሙሉ በሙሉ ላናውቅ እንችላለን። በሰዎች ልብ ውስጥ ያሉትን ውስጣዊ ዓላማዎች ሁሉ እንደማናውቅ ደግሞ የተረጋገጠ ነው። በአንድ ወንድም ላይ ክፉ መናገርና በከፊል በምናውቀው መረጃና ምናልባትም ርኅራኄ በጎደለው ውስጣዊ ዓላማ በወንድም ላይ መፍረድ እርሱንም እግዚአብሔርንም መበደል ነው። ፈራጆች ለመሆን አልተጠራንም፤ ፈራጅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱ ታጋሽና የሰዎችን አሳብ የሚረዳ ነው፤ ፍርዱም ጻድቅና ቅዱስ ነው፤ ስለዚህ ጉዳዩን ለእርሱ ልንተው እንችላለን።

ቅዱሳን እርስ በእርሳቸው በጦርነት ላይ መሆናቸው፥ መሪ በመሪ ላይ፥ ቤተ ክርስቲያን በሌላ ቤተ ክርስቲያን ላይ፥ ማኅበር በማኅበር ላይ መዝታቸው የሚያሳዝን ነገር ነው። ዓለም እነዚህ ሃይማኖታዊ ጦርነቶች በመመልከት «እርስ በእርሳቸው እንዴት እንደሚጣሉ ተመልከቱ» ይላል። በዚህ ምክንያት ኢየሱስ የሚከተለውን ጸሎት ጸለየ፡- «ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ . . . አንተ እንደላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም ባንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ» (ዮሐ. 17፡21)።

ታዲያ፥ እርስ በርሳችን በጦርነት የሆንበት ምክንያት ምንድን ነው? የአንድ ቤተሰብ አካል ሆነን፥ አንድ አዳኝ እያመንን፥ አንዱ መንፈስ በውስጣችን አድሮ፥ እርስ በእርስ ግን እንጣላለን። ለምን? ያዕቆብ ይህንን ጥያቄ እየተካሄደ ስላለ ሌላ ሁለተኛ ጦርነት በመናገር ይመልሰዋል።

በውስጣችን የሚካሄድ ጦርነት (4፡1-3)

«በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደለምን?» (ያዕ. 4፡1)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚካሄዱ ጦርነቶች ቀስቃሹ በልባችን ውስጥ የሚካሄደው ጦርነት ነው። «ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኝነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ፥ አትመኩ፤ በእውነትም ላይ አትዋሹ። ...ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሥራ ሁሉ አሉና» (ያዕ. 3፡14-16)።

የጎጢአት መሠረታዊ ይዘቱ ራስ ወዳድነት ወይም ስስታምነት ነው። ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የጣሰችው የዛፍን ፍሬ በመብላት እንደ እግዚአብሔር ብልህ ለመሆን ፈልጋ ነበር። አብርሃም ግራ ሚስቱ ሆና ሳለች እኅቴ ናት በማለት የዋሸው በራስ ወዳድነት ሕይወቱን ለማዳን ስለፈለገ ነበር (ዘፍ. 12፡10-20)። ለእስራኤል በሙሉ ሽንፈት ምክንያት የሆነውን ኃጢአትን ያደረገው ከኢያሪኮ ከተበዘበዘው ምርኮ በራስ ወዳድነት ሸሽጎ በመውሰድ ነበር (ኢያሱ 7)። «እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ» (ኢሳ. 53፡6)።

ብዙ ጊዜ ሃይማኖታዊ ጠቦቻችንን «በመንፈሳዊ» ሽፋን ሸፍነን እናቀርባቸዋለን። እውነቱ በሙሴ ሥልጣን ላይ መቅናታቸው ሆኖ ሳለ ስለ ሙሴ ሚስት እንዳጉረመረሙት እንደ አሮንና ማርያም ሆነን እንቀርባለን (ዘኁ. 12)። ወይም ደግሞ የሚፈልጉት እውነተኛው ነገር የክብርን ስፍራ ማግኘት ሆኖ ሳለ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ልዩ ስፍራ የፈለጉ ሆነው እንደቀረቡ እንደ ያዕቆብና ዮሐንስ እንሆናለን (ማር. 10፡35-45)። በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ውስጥ የራስ ወዳድነት ውጤት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚደርስ ጠብና መለያየት ነው። የማርያም ኃጢአት የእስራኤል ሕዝብ የወደፊት ጉዞ ለአንድ ሳምንት ሙሉ በሙሉ እንዲቆም ምክንያት ሆኖ ነበር።

የራስ ወዳድነት ፍላጎቶች አደገኛ ነገሮች ናቸው። ወደተሳሳቱ ተግባራት ይመራሉ፤ «ትገድላላችሁ በብርቱ ትፈልጋላችሁ» (ያዕ. 4፡2)። ወደተሳሳተ ጸሎት እንኳ ሊመሩ ይችላሉ። «ትለምናላችሁ፥ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም» (ያዕ. 4፡3)። ጸሎታችን የተሳሳተ በሚሆንበት ጊዜ የክርስትና ሕይወታችን በሙሉ የተሳሳተ ይሆናል። የጸሎት ዓላማ ምን እንደሆነ በሚገባ ተነግሮአል፡-የሰው ፈቃድ በሰማይ እንዲከናወን አይደለም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር እንዲሆን ነው።

ከአሥርቱ ትእዛዛት የመጨረሻው «አትመኝ» የሚል ነው። ይህንን ትእዛዝ መጣስ ግን የቀሩትን ዘጠኙን እንድንጥስ ሊያደርገን ይችላል። ምኞት ሰውን እንዲገድል፥ እንዲዋሽ፥ ወላጆቹን እንዳያከብር፥ ዝሙትን እንዲያደርግ፥ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የእግዚአብሔርን የሥነ-ምግባር ሕጎች ሁሉ እንዲጥስ ሊያደርጉት ይችላል። የራስ ወዳድነት ኑሮና በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ ጸሎት ሁልጊዜ ወደ ጦርነት ይመራል። በውስጥ ያለ ጦርነት በመጨረሻ በውጭ ጦርነት ወደሚደረግ መምራቱ የማይቀር ነው።

በራስ ወዳድነት ፍላጎታቸው የተነሣ ከራሳቸው ጋር በጦርነት ላይ ያሉ ሰዎች ምንጊዜም ደስተኛ አይደሉም። በሕይወት ጨርሶ ደስ አይሰኙም። ስለተቀበሉት በረከት ከማመስገን ይልቅ፥ ስላልተቀበሉት በረከት ያጉረመርማሉ። ከሌሎች ሰዎች ጋር ተስማምተው መኖር ጨርሶ አይችሉም፤ ምክንያቱም ሌሎች ሰዎች ባላቸውና በሚያደርጉት ነገር ሁልጊዜ ይቀናሉ። እውነተኛው ችግራቸው ያለው በራሳቸው ልብ ውስጥ ሆኖ እያለ ሁልጊዜ ሕይወታቸውን የሚለውጥ «አንድ ተአምራዊ» ነገርን ይፈልጋሉ።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጸሎትን የእውነተኛ ፍላጎታችንን መሸፈኛ ካባ እናደርገዋለን። ክርስቲያን ሊጠቀምባቸው ከሚችሉ የስሕተት መሸፈኛዎች አንዱ «በጉዳዩ ጸልዩበት ነበር» የሚል ቃል ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ በመፈለግ ፈንታ፥ እግዚአብሔር ማድረግ አለበት ብለን የምናስበውን ነገር እንነግረዋለን። ያንን ነገር ባይፈጽምልን በእርሱ ላይ መቆጣት እንጀምራለን። ይህ በእግዚአብሔር ላይ የገለጥነው ቁጣችን ከውስጣችን ሞልቶ ይወጣና በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ መቆጣት እንጀምራለን። በእግዚአብሔር ላይ ያለመታመናቸውንና መቆጣታቸውን በቤተ ክርስቲያን አባላት ላይ የገለጹ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን መከፋፈልን ፈጥረዋል። ሰዎች የራሳቸውን ልብና በውስጣቸው የሚካሄደውን ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ጦርነት ቢመለከቱ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ቤተሰብ ዘንድ ያለው ችግር በተቃለለ ነበር።

እግዚአብሔር ሲፈጥረን በውስጣችን የተለያዩ ነገሮች በውሕደት አካትተን እንድንይዝ አድርጓል። በውስጣችን አእምሮ፥ ስሜትና ፈቃድ በአንድነት ይሠራሉ። ያዕቆብ በውስጣችን ከራሳችን ጋር ጦርነት ስለሚፈጠርበትና በዚህም ምክንያት እርስ በእርሳችን ስለምንፈጥረው ጦርነት በተከታታይ ይገልጻል።

ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ጦርነት(4፡4-10)

የውጫዊም ሆነ የውስጣዊ ጦርነት መሠረታዊ ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ዐመፅ ነው። በፍጥረት መጀመሪያ ላይ ፍጹም የሆነ የአንድነትና የስምምነት አሠራር እንመለከታለን። ኃጢአት ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ ግን ግጭትን አስከተለ። ኃጢአት ሕግ የለሽ መሆኑ ነው (1ኛ ዮሐ. 3፡4)፥ ሕግ የለሽነት ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ የተቃጣ ዓመፅ ነው።

አንድ አማኝ በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት የሚከፍተው እንዴት ነው? ከእግዚአብሔር ጠላቶች ጋር ጓደኝነት በማበጀት ነው። ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲኖረን ከተፈለገ ወዳጆች እንዳናደርጋቸው ሦስት ጠላቶችን ይጠቅሳል።

ዓለም (4፡4)፡- ያዕቆብ ዓለም ሲል ከእግዚአብሔር ተለይቶ ያለው ኅብረተሰብ ማለቱ እንደሆነ እርግጥ ነው። በኅብረተሰባችን ውስጥ ያሉ የአኗኗርና የአካሄድ መንገዶች ሁሉ ፀረ ክርስቶስና ፀረ እግዚአብሔር ናቸው። አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበር (ያዕ. 2፡23)። ሎጥ ደግሞ የዚህ ዓለም ወዳጅ ነበር። የሎጥ መጨረሻ በሕይወቱ ውስጥ ጦርነት መከሰቱ ነበር፤ አብርሃምም ከዚህ ጦርነት ሊያድነው አስፈላጊ ሆነ (ዘፍ. 14)።

በዚህ ጥናታችን በምዕራፍ 4 እንደጠቆምኩት ክርስቲያን በዓለማዊ ጉዳዮች ተሳታፊ የሚሆነው ቀስ በቀስ ነው። በመጀመሪያ ከዚህ ዓለም ጋር ወዳጅነት ይጀምራል (ያዕ. 4፡4)። ይህም በዓለም እድፈት መበከልን ያስከትላል (ያዕ. 1፡27)። የሕይወታችን አንዳንድ ገጽታዎች የዓለም ምልክት ያረፈበትን መልክ ማሳየት ይጀምራሉ። ከዓለም ጋር የሚደረግ ወዳጅነት ዓለምን መውደድ ያስከትላል (1ኛ ዮሐ. 2፡15-17)። ይህም ዓለምን መምሰልን እጅግ ቀላል ያደርገዋል (ሮሜ 12፡2)። የዚህ አሳዛኝ ውጤት ነፍሳችን ከእሳት እንደሚድን ዓይነት ሆኖ (1ኛ ቆሮ. 3፡11-15) ቢድንም እንኳ ከዓለም ጋር ኩነኔን ማስከተሉ ነው (1ኛ ቆሮ. 11፡32)።

ከዓለም ጋር የሚደረግ ወዳጅነት ከአመንዝራነትጋር ተወዳድሮአል። አማኝ እንደ ጋብቻ በሚቆጠር ኅብረት ከክርስቶስ ጋር ተጣምሮአል (ሮሜ 7፡4)። ስለዚህ ለክርስቶስ ታማኝ መሆን አለበት። ይህንን መልእክት የሚያነብቡ አይሁዳዊ ክርስቲያኖች «የመንፈሳዊ ምንዝርናን» ምላሌነት እንደሚረዱ አንዳችም ጥርጥር የለውም።

ምክንያቱም የእግዚአብሔር ነቢያት የነበሩት ሕዝቅኤል፥ ኤርምያስና ሆሴዕ ይሁዳን ስለ ኃጢአቷ በሚገሥጹበት ጊዜ በዚሁ ቃል ተጠቅመውበት ነበር (ኤር. 3፡1-5፤ ሕዝቅኤል 23ና ሆሴዕ 1-2 ተመልከት)። የሌሎቹን ሕዝቦች ኃጢአት የተሞላበት መንገድ በመከተልና የአሕዛብን አማልክት በማምለክ የይሁዳ ሕዝብ በአምላኳ ላይ አመነዘረች።

ዓለም የእግዚአብሔር ጠላት ናት፤ ስለዚህ የዓለም ወዳጅ የሆነ ሁሉ የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን አይችልም። ያዕቆብ የሚጠቅሰው ሁለተኛው ጠላት ሥጋ ነው፤ ለሥጋ ፈቃድ የሚኖር ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን አይችልም።

ሥጋ (4፡1፥ 5)፡- ሥጋ ስንል ከአዳም የወረስነውና ለኃጢአት ምቹ የሆነው አሮጌው ተፈጥሮአችን ማለት ነው። ሥጋ ይህ ውጫዊ አካላችን ማለት አይደለም። ሥጋዊ አካላችን ገለልተኛ እንጂ ኃጢአተኛ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ውጫዊ አካላችንን እግዚአብሔርን ለማክበር ሊጠቀምበት ይችላል። አሮጌው ተፈጥሮአችን ደግሞ ውጫዊ አካላችንን ኃጢአትን ለማገልገል ሊጠቀምበት ይችላል። አንድ ኃጢአተኛ ክርስቶስን በሚቀበልበት ጊዜ በውስጡ አዲስ ተፈጥሮን ይቀበላል። አሮጌው ተፈጥሮ ግን ሊታደስም ሆነ ሊወገድ አይችልም። በዚህ ምክንያት በውስጣችን ጦርነት ይፈጥራል። «ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቃወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም» (ገላ. 5፡17)። ያዕቆብ እንዲህ ብሎ ሰይሞታል «በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደሉምን?...» (ያዕ. 4፡1)።

ለሥጋ መኖር ማለት በውስጣችን የሚኖረውን መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ማለት ነው። «ወይስ መጽሐፍ፡- በእኛ ዘንድ ያሳደረው መንፈስ በቅንዓት ይመኛል ያለው በከንቱ እንደተናገረ ይመስላችኋልን?» (ያዕ. 4፡5)። ዓለም የእግዚአብሔር አብ ጠላት እንደሆነ ሁሉ ሥጋም የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጠላት ነው። ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው የሚኖራቸው የተቀደሰ የፍቅር ቅንዓት አለ። ይህም ተገቢና ትክክለኛ ነው። መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት በቅናት ይጠብቃል። በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ ኃጢአትን በምናደርግበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ያዝናል።

አሮጌውን ተፈጥሮ ለማስደሰት መኖር ማለት በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት መክፈት ማለት ነው። «ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ

ጥል ነው» (ሮሜ 8፡7)። ሥጋ አእምሮን እንዲቆጣጠር መፍቀድ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት በማድረግ የሚገኘውን በረከት ማጣት ማለት ነው። አብርሃም መንፈሳዊ አእምሮ ነበረው፤ ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት በማድረግ ባገኘው ሰላም ደስተኛ ሆኖ ኖረ። ሎጥ ግን ሥጋዊ አእምሮ ነበረው፤ ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ በሕይወቱ ጦርነት ነበር። «ለሥጋ ግሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ግሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው» (ሮሜ 8፡6)።

ሰይጣን (4፡6-7)፡- ዓለም ከእግዚአብሔር አብ ጋር በግጭት ላይ ናት። ሥጋ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ይታገላል። ሰይጣን ደግሞ የእግዚአብሔርን ልጅ ይቃወማል። ትዕቢት የሰይጣን ትልቁ ኃጢአት ነበር። ስለዚህ ከአዳኙና ከቅዱሳን ጋር በሚዋጋበት ጊዜ የሚጠቀምበት ዋና የጦር መሣሪያ ትዕቢት ነው። እግዚአብሔር ትሑቶች እንድንሆን ይፈልጋል፤ ሰይጣን ደግሞ ትዕቢተኛ ወይም ኩሩ እንድንሆን ይፈልጋል። ሰይጣን ለሔዋን ተስፋ የሰጣትና ያመነችው ነገር «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ» የሚለውን ተስፋ ነበር። አዲስ ክርስቲያን በመንፈሳዊ የአመራር ስፍራ ላይ ሊቀመጥ አይገባም። «በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፥ አዲስ ክርስቲያን አይሁን» (1ኛ ጢሞ. 3፡6)።

እግዚአብሔር በጸጋው እንድንታመን ይፈልጋል። ጸጋውን የበለጠ ይሰጠናል ዲያብሎስ ግን በራሳችን እንድንታመን ይፈልጋል። ሰይጣን «እራስህ ሥራው» ይለናል። እራሳችንን ከፍ አድርገን እንድንመለከትና ነገሮችን ሁሉ በራሳችን መንገድ እንድናደርግ ያበረታታናል። ስለ ሰይጣን ዕቅዶች ኢየሱስ ቢያስጠነቅቅም ጴጥሮስ በሰይጣን ወጥመድ ወደቀና ሰይፉን በመምዘዝ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በራሱ መንገድ ለመፈጸም ሞከረ። ያደረገው ነገር እንዴት አደገኛና ክፉ ነበር!

በአሁኑ ጊዜ በየአብያተ ክርስቲያናችን ካሉት ችግሮች አንዱ በቂ አገልጋዮች ሳይኖሩ እጅግ ብዙ ባለዝናዎች መኖራቸው ነው። ክርስቲያን ሠራተኞች ከሚገባ በላይ ጎልተው በመታየታቸው ለእግዚአብሔር ክብር እጅግ አነስተኛ ቦታ ብቻ ይቀራል። ሰው ስለ ራሱ የሚመካበትና የሚኮራበት አንዳችም ነገር የለውም። በእኛ ውስጥ አንዳችም በጎ ነገር የለም (ሮሜ 7፡18)። በክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ የእርሱ ልጆች የሚያደርገንን «መልካም ነገር» በእኛ ውስጥ ያደርጋል (2ኛ ጢሞ. 1፡6፥ 14)።

ከእግዚአብሔር ሊለዩን የሚፈልጉ ሦስት ጠላቶች፡- ዓለም፥ ሥጋና ሰይጣን ናቸው። እነዚህ ጠላቶች ከቀድሞው የኃጢአት ሕይወታችን የሚያቆጠቁጡ ናቸው (ኤፌ. 2፡1-3)። ክርስቶስ ከእነዚህ ጠላቶች ነፃ ቢያወጣንም እስካሁንም ድረስ እያጠቁን አሉ። ጥቃታቸውን ልናሸንፍ የምንችለው እንዴት ነው? የእግዚአብሔር ወዳጆችና የዓለም፥ የሥጋና የሰይጣን ጠላቶች መሆን የምንችለው እንዴት ነው? ከጦርነት ይልቅ በሰላም በመኖር ደስ እንድንሰኝ ያዕቆብ ሦስት ትእዛዛትን ይሰጠናል።

ለእግዚአብሔር ተገዙ (4፡7)፡- ይህ ሐረግ የወታደር ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም «በተገቢው የማዕረግ ስፍራህ ተሰለፍ» ማለት ነው። አንድ ዝቅተኛ ማዕረግ ያለው ሰው እንደ ጄኔራል እሆናለሁ ቢል ውጤቱ ችግር ነው። የተሟላ ድል ለማግኘት ዋናው መሠረታዊ ጉዳይ ለአለቃ መገዛት ነው። ለእግዚአብሔር ያልሰጠነው ምንም ክፍል ቢኖር በሕይወታችን ሁልጊዜ ጦርነት ይሆናል። እራሳቸውን ያልሰጡ ክርስቲያኖች ከራሳቸውም ሆነ ከሌሎች ጋር መኖር የማይችሉት ለዚህ ነው።

ጳውሎስ በኤፌ. 4፡27 ላይ ሲያስጠነቅቅ «ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት» ብሎአል። ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር ለመዋጋት በእኛ ሕይወት ውስጥ መረማመጃን ይፈልጋል፤ እኛም ያንን መረማመጃ እንሰጠዋለን። ሰይጣንን የምንቃወምበት መንገድ እራሳችንን ለእግዚአብሔር በማስገዛት ነው።

ንጉሥ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ካመነዘረና ባሏን ከገደለ በኋላ ለአንድ ዓመት ያህል ኃጢአቱን ደበቀ። በእርሱና በእግዚአብሔር መካከል ጦርነት እንደነበረ ዳዊት ተናግሯል። መዝሙረ ዳዊት 32 ና 51ን በማንበብ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር በጦርነት በማሳለፉ የከፈለውን ከፍተኛ ዋጋ መመልከት ይቻላል። በመጨረሻ ዳዊት ራሱን ለእግዚአብሔር ባስገዛ ጊዜ ሰላምና ደስታን አገኘ። ይህንኑም በመዝሙር 32 እና በመዝሙር 51 ላይ ይገልጸዋል። እራስን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት በፈቃድ የሚፈጸም ተግባር ነው። «የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቅድ ይሁን» ማለት ነው።

ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ (4፡8)፡- ይህንን የምናደርገው እንዴት ነው? ኃጢአታችንን በመናዘዝና እንዲያነጻን በመጠየቅ ነው። «እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብ ያላችሁ እናንተ፥ ልባችሁን አጥሩ።» አንጹ ተብሎ በዚህ ስፍራ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል ስለ ቅድስና አካሄድ የሚናገር ነው። ይህ በቁጥር 4 ላይ

የተጠቀሰውን «የመንፈሳዊ ምንዝርናን» አሳብ በማነፃፀር የሚያቀርብ ነው።

ዶክተር ኤ. ደብሊው. ቶዘር ከመጻሕፍቶቻቸው በአንዱ ላይ «መቅረብ መምሰል ነው» (*Nearness is Likeness*) በሚል ርእስ ሰፊ ጽሑፍ ጽፈዋል። እግዚአብሔርን በመምሰል እያደግን በሄድን ቁጥር ለእግዚአብሔር ቅርብ እየሆንን እንሄዳለን። እኔ በሳሎን ውስጥ ከድመቴ ጋር ቁጭ ብልና ባለቤቴ ግን ያለችው 7 ሜትር ርቃ በኩሽና ውስጥ ቢሆንም ቅርበቴ ከድመቷ ይልቅ ለባለቤቴ ነው። ምክንያቱም ድመቷ እኔን የምትመስልበት አንዳችም ነገር የለም። በጣም ጥቂት የጋራ የሆነ ነገር ብቻ ነው ያለን።

እግዚአብሔር ከእኛ እንዲርቅ የሚያደርገውን በሕይወታችን ያለውን ኃጢአት በምናስወግድበት ጊዜ በጸጋው ወደ እኛ ይቀርባል። እኛን ከሌላ ከማንም ጋር ሊጋራ አይሻም። በእኛ ላይ ሙሉ ቁጥጥር ሊኖረው ይገባል። በሁለት አሳብ የሚወላውል ክርስቲያን ጨርሶ ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ አይችልም። እንደገና አብርሃምና ሎጥን ልናስታውስ እንችላለን። አብርሃም ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ስለ ሰዶም ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገረ (ዘፍ. 18፡23-33)። ሎጥ ግን ወደ ሰዶም በመግባት የእግዚአብሔርን በረከት ሁሉ አጣ።

በጌታ ፊት ራስን ማዋረድ (4፡9-10)፡- በውጫዊ ገጽታ እራስን ለእግዚአብሔር ያስገዙ መስለው በውስጥ ግን እራስን በትሕትና ዝቅ ሳያደርጉ መኖር ይቻላል። እግዚአብሔር የትዕቢትን ኃጢአት ይጠላል (ምሳሌ 6፡16-17)። ስለዚህ ትዕቢት የነፋው አማኝ ትሑት እስኪሆን ድረስ በተገቢ የሥነ-ሥርዓት ቅጣት ያስተምረዋል። ኃጢአትን እንደ ቀልድ የማየት እንዲያውም በኃጢአት ላይ የማፌዝ ዝንባሌ ይታይብናል (ላታችን ወደ ኃዘን ሊለወጥ ይገባዋል)። ኃጢአት እጅግ ከፉ ነገር ስለሆነ የእውነተኛ ትሕትና አንዱ ምልክት የኃጢአትን አደገኝነት ተገንዝቦ አለመታዘዝን ለማስወገድ ጉዳዩን በሚገባ መያዝ ነው። «የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም» (መዝ. 51፡17)።

አንዳንድ ጊዜ አማኝ «እግዚአብሔር ሆይ ትሑት አድርገኝ» የሚል ጸሎት ሲጸልይ ይሰማል። እንደዚህ ዓይነት ጸሎት መጸለይ አደገኛ ነገር ነው። እራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት ትሑት አድርገን ኃጢአታችንን በመናዘዝ በኃጢአታችን እጅግ በማዘን እርግፍ አድርገን ብንተወው ይሻላል። «ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ»

(ኢሳ. 66:2)። «እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፥ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል» (መዝ. 34:18)።

እነዚህን ሦስት ትእዛዛት ብንከተል እግዚአብሔር ወደ እኛ ይቀርባል፤ ያነጻናል፤ ይቅርም ይለናል፤ ጦርነቶቹም ያቆማሉ። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ካለን ከራሳችንና ከሌሎችም ጋር ሰላም ይኖረናል። «የጽድቅም ሥራ ሰላም፥ የጽድቅም ፍሬ ለዘላለም ጸጥታና መታመን ይሆናል» (ኢሳ. 32:17)።

የሕይወትህን አስተዳደር በእግዚአብሔር ትከሻዎች ላይ ተውና እርሱ የሰላም ልዑል ይሁንልህ (ኢሳ. 9:6)።